ሊጠብቅ የሚቻለው አምላክ እግዚአብሔር ነው። በተለይ የስሕተትን ትምህርትና አስተማሪዎች ለመቃወምና ለማስጠንቀቅ ተጻፈ መልእክት ውስጥ እንዲያ ያለ ተስፋን ማስፈር የአማኞችን ልብ በችግሮች ብዛት እንዳይርድ የሚደግፍ እውነት ነው። በእርሱ ከታመንን በእጆቹ መዳፍ ውስጥ ነን፤ ከዚያ የሚያወጣን ማንም የለም። እግዚአብሔር በዚህች ምድርና በዚህ ዕድሜ ብቻ ቅዱሳንን ሳይሰናከሉ የሚጠብቅ ብቻ አይደለም። ከዚህም ባሻገር በክብሩ ፊት በደስታ ነውር የሌላቸው አድርጎ የሚያቆም አምላክም ነው። ክብሩ በታላቅ ግርማ ሊፈርድ በዙፋኑ የሚቀመጥበት ነው። ቅዱሳኑ በዚያ ክብር ፊት ያለ ነውር ሆነው በደስታ ይቆማሉ። ደስታ የተሰኘው ቃል ታላቅ ደስታ ወይም ሐሴት ነው።

ይህን ለሚያደርገው ጌታ፥ 'ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፥ አሜን።' አሜን።





# ምዕራፍ አራት

# አስተውሎት

በዚህ ክፍል የተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች ተካትተዋል። እነዚህ ሊዘነጉ የማይገባቸው፥ ብዙውን ጊዜ ግን የማይስተዋሉ ነጥቦች ናቸው። አንዳንዶቹ መስተዋል የተገባቸው ገንቢ ነጥቦች ሲሆኑ ሌሎቹ የተለያዩ የስሕተት ገጽታዎች ናቸው። እነዚህ ነጥቦች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በአገራችንም ለሚታዩት ለተሳሳቱ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎሞችና እነዚህ አተረጓጎሞች በብዛት በሚስተዋሉባቸው ካሪዝማዊ ልምምዶችና ችግሮች መንገድ የጠረጉ፥ በር የከፈቱ፥ ወይም ከተከፈተ በኋላ የገቡ ናቸው። እኒህን ነገሮች ማወቁም ማስተዋሉም ለመጠንቀቅም ሌሎችን ለማስጠንቀቅም ጠቃሚ ይሆናሉ።

## ከስሕተቶች ጀርባ

መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳቱ መንገዶች የሚተረጉሙ በርካታ አገልጋዮች መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው የተጻፈው እውነት ይልቅ በቀጥታ መንፈስ ቅዱስ እንደተናገራቸው አድርገው የሚያቀርቡት ማብራሪያ ነው። መንፈስ ቅዱስ ቃሉም እንዲጻፍ ያደረገና የጻፉትንም የመራ አምላክ ነውና በቃሉ ውስጥ ያለውን እውነት ሊከስትና ሊያብራራ ይችላል። ግን፥ እነዚህ ሰዎች የሚሰጡት ትርጓሜ በግልጽ ከተጻፈው ጋር የሚጋጭ ከሆነ ቆም ብሎ ማስተዋሉ የሚበጅ ነው። መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያልሠራበት ዘመን አልነበረም። አለ ካልን አባባላችን አንጻራዊና መጠናዊ ብቻ ነው፤ ሰው ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ከቶም ሊድንና ደኅንነትን ሊለማመድ አይችልምና። ያለ እርሱ እርዳታም ትልቅ ወይም ትንሽ ፍሬያማ የወንጌል ተግባርን ሊያከናውን አይችልም። ያለእርሱም እርዳታ በመከራና ስደት ውስጥ ጸንቶ ማለፍ አይቻልም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፥ ጨለማው ዘመን ተብሎ በሚታወቀው መካከለኛው ዘመንም እንኳ ውብ ሥራዎች ተሠርተዋል። ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ በተለያዩ ቦታዎች ህያው ዘአካልነትዋን በድርጅትነት፥ መንፈሳዊነትዋንም በዓለማዊነትና በፖለቲካ የለወጠችባቸው ጊዜያት አልጠፉም። አሁንም አለ፤ ወደፊትም ይኖራሉ። ይህንን እየተቃወሙ የተራመዱ፥ ተቃውሞው ነጥሮ በላያቸው ወድቆ የተጨፈለቁም አሉ። ከግለ

ሰብ አማኝና አገልጋይ እስከ ቡድኖች፥ እስከ ማኅበራትም የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትናን አርማ ይዘው የተነሡ ኖረዋል። ይህን ሁሉ የሆኑትና ያደረጉት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ነው። ታሪካዊውን ክርስትና ትተን ዕለታዊውን የነፍስ ወከፍ አማኝ ሕይወት እንኳ ብንመለከት ከደኅንነታችን ጀምሮ የየቀኑ ኑሮና እርምጃ ያለ መንፈስ ቅዱስ አስቻይነት ከቶም ሊደረግ የማይቻል ነው።

አንዳንድ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችና ንቅናቄዎች ዘርፈ ብዙዎች ናቸው። አንዳንዶቹ በአንድ ገጽታ ብቻ ላይ ያተኩራሉ፤ ከዚህም ተነሥቶ በአንድና ነጠላ ገጽታቸውም ይታወቃሉ። ጴንጤቆስጣዊው እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሊቃውንት ዘንድ በሁለት እንደሚከፈልና ሁነኛውና ዓይነተኛው *Classical Pentecostalism* እንደሚባል፥ ከ20ኛው ምዕት ዓመት ወዲህ የሆነው ዘመነኛው ደግሞ *Neo-Pentecostalism* እንደሚባል *በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች* መጽሐፍ አውስቻለሁ። ካሪዝማዊ ንቅናቄ የዘመነኛው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ውጤት ነው። ዘመነኛው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ሲጀምር ይህኛው ካሪዝማዊው እንቅስቃሴ ደግሞ እስከ ክፍለ ዘመኑ አጋማሽ ድረስ እንደ ንቅናቄ አልነበረም። ሁነኛው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ በአማኞች አገልጋይነትና በጸጋ ስጦታዎች ገቢራዊነት ላይ በማተኮር ጤናማ አስተዋጽዖን በተሐድሶው ዘመንና ከዚያም በኋላ አድርጎአል።

ዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴና ተከታዩ ካሪዝማዊ ንቅና ቄ ግን በአንድ ልምምድና ስጦታ ብቻ ላይ ያተኮረ ነበረ ማለት ይቻላል። ያም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና የዚህም ምልክቱ እንደሆነ የሚነገረው የልሳን ስጦታ ናቸው። እንደ ንቅናቄው ትምህርት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማኝ ከዳነ በኋላ የሚጠመቀው ጥምቀት ሲሆን የመጠመቁ ምልክትም በልሳኖች መና ገሩ ነው። የተጠመቀ ሁሉ በልሳን ይናገራል፤ የማይናገር ሁሉ ደግሞ አልተጠመቀም ማለት ነው። የቃሉ ትርጉም የሚተረጎመው በአብዛኛው የገነነ ልምምዳዊነትን ተከትሎ ሲሆን ቀጥሎም መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ታሪክ ከተጻፈበት አስተምህሮታዊ ሳይሆን ታሪካዊ ይዘት ካለው ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው። ብዙውን ጊዜም የዚህ ቃል ትርጉም በቀጥታ የሚገኝበት 1ቆሮ. 12፥13 ተገቢ ትኩረት አይሰጠውም።

መንፈሳዊ ልምምዶች ቃሉን በመከተል ፈንታ ቃሉ መንፈሳዊ ልምምዶችን እንዲከተል የሚደረጉባቸው አተረጓጎሞች በዚህ ዘመን በብዛት እየታዩ ናቸው። እንዲህ ያሉ የአተረጓጎም ስሕተቶች በተለያዩ ስፍራዎች የሚታዩ ቢሆኑም በዘመናዊዎቹ የመነቃቃትና ተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በብዛት ይታያሉ። ስለዚህም ነው በዚህ ክፍል በብዛት የሚጠቀሱት። በካሪዝማዊ ንቅናቄ ውስጥ





ከአስተምህሮቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ይልቅ ከልምምዶቹ በኋላ አስተምህሮቶቹን መንደፍ በጉልህ ይታያል። ለዚህ ነው የንቅናቄው ስነ መለኮት ሽንቁር የሆነውና ብዙ ልምምዳዊ ስሕተቶች የሚገቡበት። አንዳንድ የንቅናቄው ጉልህ አስተማሪዎች እንዲያውም አስተምህሮት ወይም ዶክትሪን የሚባለውን ቃል አጥብቀው ይጠሉታል፥ ይሸሹትማል። ዶክትሪን ወይም አስተምህሮ በሥርዓት የተደራጀና የተቀናጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማለት ሆኖ ሳለ እኒህ መሪዎች ሰው ሠራሽ መጠፈሪያ አድርገው ያዩታል። በካሪዝማዊ ንቅናቄ ዙሪያ በእጅጉ የሚታወቀው ኬነት ኮፕላንድ በአንድ ስብከቱ፥ "እኔ እምነትን ነው እንጂ ዶክትሪንን አልሰብክም" ብሎ ነበር።[1] ቃሉ ግን ለራስህና <u>ለትምህርትህ</u> ተጠንቀቅ ይላል፤ 1ጢሞ. 4፥16። ዶክትሪን ማለት አስተምህሮት ወይም ትምህርት ነው። የነዚህ ሰዎች ትምህርት ከሚናገሩት ነገር ጋር የሚቃረንበት ዋና ነጥብ ዶክትሪን አናስተምርም ይበሉ እንጂ የሚጽፉትን ወይም የሚሰብኩትን ትምህርቶች ጨምቀው እርስ በራሳቸው ቢጋጩም እንኳ እንደ አስተምህሮት ቀርጸው ለተከታዮቻቸው ያስጨብጡአቸዋል።

ካሪዝማዊ ንቅናቄ ማለት ራሱ ስሙ ሰፊ የሆነውን ካሪዝማ የሚል ቃል ይያዝ እንጂ በጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ላይ ሳይሆን በአንዱ ስጦታ በልሳን ላይ ያተኮረ የልሳን ንቅናቄ ነው፤ ይህ የንቅናቄው መግቢያ በር ነውና። በሰፊና ዓለማዊ ትርጉሙ ካሪዝማ ማለት የአንድ ሰው የተለየ ችሎታ ወይም ሞገስ ማለት ነው፤ ብዙውን ጊዜ ለመሪነት የሚሰጥ ቅጽልም ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙ ደግሞ ካሪዝማ የጸጋ ስጦታ ማለት ነው። ማናቸውም መንፈስ ቅዱስ የሚያድለው በጸጋ የተገኘ ስጦታ ሁሉ ካሪዝማ ነው። እንደዚህ ትርጉም ከሄድን ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ሁሉ ቢያውቀውም ባያውቀውም፥ ቢለማመድና ቢያገለግልበትም ወይም ሳያውቀው ቀርቶ ይዞት ቢኖር የጸጋ ስጦታ ወይም ካሪዝማ አለው። ወደ ካሪዝማዊ ንቅናቄ ምንነት ስንመጣ ግን እንዲህ ይተረጎማል፤

> ይህ እንቅስቃሴ በልሳኖች የመናገር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖርና ሊታይ የሚገባው ልምምድ ነው የሚሉ ሰዎች፥ ቤተ ክርስቲያኖች እና ንቅናቄዎችን የሚያቅፍ ነው። እነዚህ ሰዎች፥ ቤተ ክርስቲያኖችና ንቅናቄዎች በጠቅላላው ከመጀመሪያው ወይም ኦርጂናሌው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ያልመነጩ ተቋሞች እና ቤተ እምነቶች ክፍሎች ናቸው።[2]

---

[1] Copeland, FFA I, side 1.

[2] Bowman p. 28.

ስለዚህ ነው ከላይ ካሪዝማዊ ንቅናቄ የልሳን ንቅናቄ ነው ያልኩት።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ራሱ ካሪዝማዊ ንቅናቄ የሚለው ቃል እየቀረ የመነቃቃትና ተሃድሶ ንቅናቄዎች *Revival and Renewal Movements* በሚለው ሰፊ እንቅስቃሴ እየተለወጠ ነው። ይህኛው ደግሞ የተሸናሸነና ሐረጉም የበዛ ነው። አንድ ሳይሆን ብዙ ነው፤ ማዕከላዊነት ያለው ሳይሆን የተበታተነ ነው፤ ተመሳሳይና ቅንጁ ሳይሆን በያይነቱና ንጥል ነው። በያይነትነቱ ግን እንደ ጴንጤቆስጣዊና ካሪዝማዊ ንቅናቄዎች ሁሉ የሚተኮርባቸው የተወሰኑ ልምምዶች ዙሪያ መሽከርከሩን አያስወግደውም። ከአንድ ወገን ሲታይ ክርስቲያናዊና መንፈሳዊ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ስሜታዊና ሰውኛ ብቻ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት የጎደላቸው ነገሮችና ልምምዶች አሉበት። ከዚህ አልፎ መስተዋል ያለበት ነገር ደግሞ ይህ ይህ እንቅስቃሴ ማኅበራዊ ወይም ፖለቲካዊ ወይም ሌላ ሳይሆን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነው። ስለዚህም ከሰው ብቻ ልምምድና ኃይል ሌላም መንፈሳዊ አሠራር ሊኖር እንደሚችል መጤን አለበት። መንፈሳዊ ሲባል የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ብቻ ሳይሆን በሚያሳስት መልክ ሰይጣናዊ ተጽዕኖም ሊኖርበት እንደሚችል መስተዋል አለበት። አንዳንዶች ካሪዝማዊ እንቅስቃሴን እንደ መነቃቃት እና ተሐድሶ *(revival and renewal)* ያዩታል ወይም ከዚያ ጋር ያመሳስሉታል። ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ከዘመናዊው የመነቃቃትና ተሐድሶ ንቅናቄዎች የተለየ ነው። በልምምድና በውጤት ረገድ ግን ሁለቱም የሚመሳሰሉባቸው በርካታ ነጥቦች አሉ። አንዳንዶች የመነቃቃት እንቅስቃሴዎችን የቀዘቀዙ ሰዎችና አብያተ ክርስቲያናትን እንደሚያሞቅና እንደሚያግል ጴንጤቆስጣዊ እሳትና መቀጣጠል ይመለከቱታል። በአመዛኙ ግን ይህኛው ከእሳቱ ይልቅ ጪሱ የበረታበት እንቅስቃሴ ነው። ከእሳቱ ሙቀት የጪሱ ማፈን ያየለበት ንቅናቄ ነው።

ለ*revival* ያለን የተለመደ ቃል መነቃቃት ነው። አሳቡ ከፍዘት መንቃትን፥ ከድካም መበርታትን፥ ከመጠውለግና ለሞት ከመቅረብ ማንሰራራትን የያዘ ነው። መነቃቃት በግልም፥ በቡድንም፥ በማኅበርም ሊከሰት የሚችል በራሱ ጤናማ የሆነ ነገር ነው። ጤናማው ክርስትና ሁሌም እንደተነቃቁ መኖር ነው። ግን ይህ ሁሌና ለሁሉ እውነት አይሆንም። ስለዚህ ጌታ ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን፥ "ሊሞቱ ያላቸውን የቀሩ ነገሮች አጽና" እንዳለው (ራእ. 3፥2) በግልም በወልም በሕይወት ውስጥ የሚመነምኑና ሊጸኑ የተገባቸው አያሌ ነገሮች ይኖራሉ። እንግዲህ ፪መጀመሪያ ከመነቃቃት በፊት የዚህ ቅድመ ሁኔታ መኖር የግድ አስፈላጊ ነው። ቀጣዩ ነጥብ ጤናማ መነቃቃት በሕይወት ውስጥ የሚከሰትበት ሁኔታ ነው። መነቃቃት የሚመጣበት ቀመር የለውም፤ በጸሎትም በድንገትም፤ በትምህርትም በስብከትም፤ በግልም በወልም ሊከሰት ይችላል።





ውጤቱም በአንድ ወይም በሌላ መንፈሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ወይም ተግባር ላይ ያተኮረ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፥ የወንጌል ስርጭት፥ የቅድስና ኑሮ፥ ሠናይ ምግባር፥ ወዘተ።

ጤናማና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነቃቃት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችና ልምምዶችን አይጋብዝም፤ አያሰራጭምም። ዘመናዊዎቹ የመነቃቃትና ተሐድሶ ንቅናቄዎች ግን ከቃሉ ጋር በተጋጩ በርካታ ልምምዶች አሸንክታብ የተሸለሙ ናቸው። አንዳንድ የመነቃቃት አስተማሪዎች ከመንፈሳዊ መነቃቃት ጋር የሚመጡ ጉድፎች ሁሌም ከመነቃቃት ንቅናቄዎች ጋር አብረው እንደተፈጠሩ ያህል የማይለያዩ ነገሮች እንደሆኑና መነቃቃቱን ከተቀበልን ከነዚህ ነገሮች መጽዳት እንደማንችል አድርገው ያስተምራሉ። አንድ መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል፥ "ሪቫይቫል ጽዱ ነገር አይደለም። መልካም የሆነው መልካም ካይደለው ጋር ተቀይጦ የሚገኝበት ነገር ነው። . . . ይህ ርዕስ የተጻፈው ሪቫይቫል የብዙ ምዕመናን ልብ የማያርፍባቸውን የተለያዩ ልምምዶች ይዞ እንደሚመጣ ለማስጠንቀቅ ነው።"[3] በምዕራፍ ሁለት የተጠቀሰው ሰባኪም ሪቫይቫልን ሁሉን አግበስብሶ ከሚመጣ ድፍርስ ወንዝ ጋር በማመሳሰል ድፍርስ ነው ብለን መሸሽ እንደማይገባንና ወደ ወንዙ መግባት እንደሚያሻን ሰብኮአል። እንግዲህ የመነቃቃት ንቅናቄዎችንና ልምምዶቻቸውን ስንቀበል በጅምላና እንደታሸጉ ነው ማለት ነው። እሽጉ ሲከፈት ጥሩ ያልሆኑ ነገሮች አሉበት፤ ግን የእሽጉ አንድ ብልት ስለሆኑ የግድ አብረው የሚመጡ ናቸውና መሸሽ አንችልም ማለት ነው።

መስተዋል ያለበት ግን ምንም ዓይነት ልምምድ እና ማንም አስተማሪ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በላይ ዋጋ ከጠየቀ ጭፍንና ስሕተት መሆኑ ነው። ከካሪዝማዊ እንቅስቃሴ እንዲሁም ከመነቃቃትና ተሐድሶ ንቅናቄዎች ውስጥ አፍላው ሞቅታ ካለፈ በኋላ ዘቅጠው የሚቀሩት ብዙዎቹ ረባሽና ጎጂ ልምምዶችና ትምህርቶች ይኖራሉ። አንዳንዶቹ ልምምዶች በጊዜ ውስጥ ሊከስሙ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ በፈረንጆች ቆጠራ በ90ዎቹ መጀመሪያና አጋማሽ እንደተከሰተው ቅዱስ ሳቅ ያሉት ከጥቂት ዓመታት ያልዘለሉ ልምምዶች ናቸው። ከልምምዶቹ ጋር የተጣበቁት የትምህርቶቹ ጎጂነት ግን ተላላፊ ነው። ሙልጭ ያለ ስሕተት ሆኖ እንኳ አስተማሪዎቹ እንደ ታላላቅ ነቢያት፥ ትምህርቶቻቸውም በንቅናቄዎቹ መሪዎች እንደታላላቅ አስተምህሮዎች የሚወሰዱበት ሁኔታ ጥቂት አይደለም። ለምሳሌ፥ ዊልያም ብራንሃም የኋለኛው ዝናብ ንቅናቄ *(Latter Rain Movement)* እየተባለ በሚታወቀው የካሪዝማዊ ንቅናቄ ቅርንጫፍ ሰፊ ሚና የተጫወተ ሰው ነበር።

---

[3] በቀለ ወልደ ኪዳን፥ ገጽ 203።

ብራንሃም በዚህ ዘመን ያሉ የንቅናቄው መሪዎች እንደ ታላቅ ነቢይ የሚያዩትና ራሱም ራሱን እንደ ኤልያስና በራእ. 3፥14 እና 10፥7 እንደተጠቀሱት ምስክርና ሰባኪ የቀባ ሰው ነው። እንደ ነጮች ቆጠራ በ1977 አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በምትቆጣጠራት የዓለም ቤተ ክርስቲያናት ጉባዔ *(World Council of Churches)* እንደሚዋጡ፥ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን እንደምትነጠቅና ዓለምም እንደሚፈረድባት ተናግሮ ነበር። ይህ ከመሆኑ ከ12 ዓመታት በፊት ራሱ ብራንሃም ሲሞት ተከታዮቹ ከሦስት ቀናት በኋላ ከሞት እንደሚነሣ ወይም ከዚያ በኋላ በትንሣኤ ተነሥቶ እንደሚያገለግል ይጠብቁ ነበር። ብራንሃምን እና ትምህርቶቹን ጠለቅ ብለን ስንመለከት ግን እጅግ ብዙ ስሕተቶች አሉበት። ጥቂቶቹ ይህ ሰው የማንም ቤተ እምነት አባል መሆን አጥብቆ ከመጥላቱ የተነሣ ቤተ እምነት የአውሬውን ምልክት መቀበል ነው ይል ነበር። ከዚህም ሌላ ትምህርተ ሥላሴ የሰይጣን ትምህርት ነው፤ ስለዚህ ጥምቀት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሳይሆን በኢየሱስ ስም ብቻ መሆን አለበት ብሎ ያስተምር ነበር።[4] ከዚህ ሌላ ብራንሃም የሔዋን ኃጢአት ፍሬውን መብላትዋ ሳይሆን ከእባብ ጋር ግብረ ሥጋ መፈጸሟ እንደሆነ፤ አንዳንድ ሰዎች ከዚህ ግንኙነት የተወለዱና ለሲኦል የታጩ እንደሆኑ፤ የእርሱን ትምህርት የሚቀበሉ የክርስቶስ ሙሽራ ሲሆኑ በቤተ እምነቶች ውስጥ ከሚገኙት ውስጥ ጥቂት የሚድኑ ቢኖሩ እንኳ በታላቁ መከራ ውስጥ አልፈው እንደሚድኑ አስተምሮአል።[5] እንዲህ ያሉት ትምህርቶች ከመስመር በወጡ የግል የአተረጓጎም ሕግጋት የተፈጠሩ ቢሆኑም የዘመናዊው ካሪዝማዊ ንቅናቄ አባት የሚባለውን ኬነት ሄገንን እና ከብራንሃም ጋር አብሮ ያገለገለውን ፖል ኬይንን ጨምሮ በካሪዝማውያን መሪዎች ዘንድ የብራንሃም ትምህርቶችና ትንቢቶቹ ሁሉ ዛሬም እንደ እግዚአብሔር መልእክት ይወሰዳሉ።[6] በብራንሃም አገልግሎት ውስጥ በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በርካታ ፈውሶች መኖራቸው ይወሳል። ይሁንና፥ ዲ አር መኮኔል የተባለ ጸሐፊ እንደሚያወሳው ትምህርቶቹ ከእውነት እየራቁ መጥተው ወደ ሕይወቱ ፍጻሜ ፈጽሞውኑ ግልጽ የስሕተት ትምህርት ሆነው ነበር። ጸሐፊው፥ "ምንም እንኳ የብራንሃም ምሳሌነት ወደ አንድ ጫፍ የራቀ ቢሆንም፥ ይህ የተአምራትና የፈውሶች አገልግሎት የትምህርት ትክክለኛነትን ፈጽሞ እንደማያረጋግጥ ያሳያል" ይላል።[7] ታድያ እነዚህንና የመሳሰሉትን ከመነቃቃት ንቅናቄዎች

---

[4] Branham, p. 606-7.
[5] Burgess etal., p.96
[6] Ibid.
[7] McConnell, p. 166.





'ወንዞች' ጋር የሚመጡ የአስተምህሮት ጉድፎችን አብረው የሚመጡ ስጦታዎች አድርገን በዝምታ መቀበል አለብን? የለብንም። ሰባኪዎችም ስለሚወደዱና ስለሚታመኑ የሚናገሩት ሁሉ ሳይመረመር በጅምላ መገዛት የለበትም።

በመነቃቃት ንቅናቄዎችም ሆነ እነዚህ ነገሮች በሌሉበት ጊዜ የስሕተት ልምምዶችና ትምህርቶች አይኖሩም ማለት አይደለም። ይኖራሉ። ከነዚህ ስሕተቶች ጀርባ የተለያዩ ግፊቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በአጠቃላይ እይታ እኔ ሦስት ነገሮች ያሉ ይመስለኛል። ከዚያ ሊበልጡም ይችላሉ ብዬ እገምታለሁ። እኔ ግን በሦስት ትልልቅ መደቦች አስቀምጣቸዋለሁ። ሦስቱም በደረጃቸው እነዚህ ና ቸው፥

1፥ ንጹሕ ሕሊና። ይህ ካለማወቅ የተነሣ መሳሳት ነው። እንደሚታወቀው ሕሊናችን ቀድሞ ያወቅነው፥ የተረዳነው አንድ ነገር ትክክል መሆንና ያለመሆኑን ይነግረናል እንጂ አዲስ ነገር አያስተምረንም። አንዳንድ ሰዎች ስሕተትን ትክክል ነው ብለው ከተማሩ አእምሮአቸው በስሉ እስኪደርሱበት ድረስ በንጹሕ ሕሊና ያንን ነገር ትክክል ነው ብለው ይቀበሉታል፤ ምንም ጥያቄ ሳይፈጥርባቸው ይኖሩበታል፤ ያስተምሩታልም። እንደዚያ ተደርጎ ስለተነገራቸው ተቀበሉት እንጂ ነገሩ ግን ትክክል ላይሆን ይችላል። ይህ ካለመማርና ካለመረዳት የሚመጣ የየዋኀነት ስህተት ነው። ይህ ያለመረዳት ወይም የንጹሕ ሕሊና ስሕተት ትምህርትን ካለማግኘት የተነሣ በሰዎች ውስጥ ሊኖር የሚችል መንፈሳዊ ያለመብሰልም ነው። ለእነዚያ ሰዎች ያ ስሕተት ስሕተት መሆኑ ከታወቃቸውና ከእውነቱ ጋር ከተዋወቁ በኋላ እውነቱን ካልተቀበሉት የስሕተታቸው ንጹሕነቱ እዚያ ላይ ያከትማል። ከዚያ በኋላ ንጹሕ ስሕተት ሳይሆን አውቀው የሚፈጽሙት ጥፋት ነው።

ሌላው የዚሁ የንጹሕ ስሕተት ፈርጅ ነው የምለው ካለማወቅ የተነሣ የሚደረግ የተሣሣተ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ነው። የሪቫይቫልና ተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከዐውደ ምንባቡ እየተገነጠሉ የሚተረኩና የሚፈቱ፥ የማይሉትንም እንዲሉ የሚደረጉ በርካታ ክፍሎች አሉ። ይህ ሆን ተብሎ የተደረገ ካልሆነ የአፈታትን ሕግጋት ካለማወቅ የሚመጣ ችግር ነው። አንድ ሰባኪ ወይም አስተማሪ በጠቅላላው የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በግልጽ የተወሳውን እውነትና ቢያንስ መሠረታዊ የሆኑትን የስነ አፈታት ደንቦች ማወቅና መከተል አለበት። ቢችልና ሁኔታዎች ቢመቻቹለት መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ ቃሉን በጥልቀት መማርም አለበት። ይህ ካልሆነ ከአንድ ሰባኪ የመነጨ አንድ መፋለስና ስሕተት ወደ ሌላው ሰባኪና ወደ መደዴው አድማጭም የሚተላለፍ ይሆናል። ሊስተዋል የሚገባው ነገር ግን ስሕተቶቹ ከንጹሕ ሕሊና ቢመነጩም እንኳ የውጤታቸው ጎጂነት ያለመቅረቱ ወይም ያለመቀነሱ ነው። የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፎች በዚህ የስነ

አፈታት ርዕስ ላይ መጠነኛ ሐተታ ማቅረብ ነውና ይህን ችግርና መፍትሔ አሳቦች በምዕራፉ ተመልከቱ።

2፥ ጥቅም ሌላው ከስሕተት አሠራሮች ጀርባ ያለ ሌላ ኃይል ነው። በጥቅም ታውረው ስተው የሚያስቱ ሰዎች አሉ። ጥቅም ሲባል መልኩ ብዙ ነው። ሥልጣን አንድ የጥቅም ፈርጅ ነው። አንዳንድ መሪዎች የሥልጣንን እርካብ ከእግራቸው ሥር ለመጠበቅና እንደተቆናጠጡ ለመቆየት ሲሉ ከተጠያቂነት በላይ የሚያደርጋቸውን ፈር ይቀድዳሉ፤ ደንብ ይደነግጋሉ። ብዙውን ጊዜ ከነበሩበት ቤተ ክርስቲያን ወጥተው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ወይም ያን መሰል ማኅበር መመሥረት ይህን የሚያደርጉበት የመጀመሪያ መረማመጃቸው ነው። ከዚህ በኋላ ሥልጣንን የብዙ የአስተምህሮታዊ ስሕተቶቻቸውና ግብረ ወጥ ገበናዎቻቸውን መሸፈኛ ያደርጉታል። ለዚህ ነው በብዙ የስሕተት ትምህርቶች ዘንድ መሪዎች እንደ መለስተኛ አምላክ የሚታዩትና የማይጠየቁት ወይም ወደ እነርሱ ለመድረስ ወይም ለመቅረብም ብዙ እርከን መወጣት ያለበት። በርካታ አዳዲስ ማኅበራት የሚመሠረቱት የመሪዎቹ ጥያቄ የማይፈታ ወይም ጥያቄዎቻቸው የማይመለስ ስለሆነ ሳይሆን ሥልጣንና ጥቅም፥ ጭፍራና አራጋቢ ፈላጊዎች በመሆናቸው ነው። እነዚህ መሪዎች ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን በገዛ እጃቸው የቀቡ ገዥዎች ናቸው። መሪዎች ሳይሆኑ ገዥዎች ና ቸው። ሥልጣናቸውን የሚጠይቅ ወይም እጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ምንም ነገር ሲነሣባቸው መታገስ አይችሉም። እንዲህ ያሉ ባለ ሥልጣኖች በአጥቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ሲፈጠርባቸው ከዚያ ችግር ለመሸሽ፥ ግን ከኖሩበት የታዋቂነት እርካብ ላለመውረድ ሲሉ በአካባቢው ወይም ከዚያ ራቅ ብለው፥ ሌላ መሰል ማኅበር ወይም በአገልግሎት ስም የሆነ አገር አቀፍ ወይም ዓለም አቀፍ ሰው ሠራሽ የሥልጣን መረብ ይዘረጋሉ። በዚህ ዘመን እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለችው አንዲትና ብቸኛ አካል ቤተ ክርስቲያን ናት፤ ይህች አካል የሥልጣኑም መግለጫና መገለጫ ናት። ለቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በመገዛት ፈንታ ቤተ ክርስቲያንን ሊገዛ የሚወድ የሥልጣን ጥም ወደ ስሕተት የሚከትት ነው።

የጥቅም ሌላው ፈርጅ ንዋይ ነው። ብልጽግናና ገንዘብ አንዳንድ ጊዜ የስሕተት ትምህርቱ አንድ ክፍል ይሆኑና ግልጽና ስውር የገንዘብ ማሰባሰቢያ መረብ ይዘረጋል። አንዳንድ መሪዎችም ጨርሶ እስከማይንቀሳቀሱ ድረስ በገንዘብ ፍቅር ገመድ እግር ተወርች ይታሰራሉ። ትንቢት የሚመስል ቃል እየተናገሩም ከጥቃቅን ቁሳቁስ እስከ ትላልቅ ንብረት ድረስ መውረስ በእነዚህ ዘንድ የሚሰማ ጉዳይ ነው። 'ጌታ ይህን ነገር (ገንዘብ፥ መኪና፥ ቤት፥ ወዘተ፥) ለእገሌ ስጥ ይልሃል' ተብለው የተወናበዱ በርካታ ናቸው። ምንም እንኳ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ቢሆንም በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት እንጂ በአሳቾች እየነሆለለ መሆን





የለበትም። እንደዚህ የሚታለሉት ሰዎች ፈጥነው ወይም ዘግይተው ወደ ጉስቁልናና ማማረር ሲወርዱ አታላዮቹ ደግሞ ደግሞ ቲኬት ያልገዙበት ቶምቦላ ይወጣላቸዋል! ጥቅም እንዲህ ነው። አንዳንድ አገልጋዮች በገንዘብ ከሚረዱአቸው ሰዎች ጉያ የማይወጡ መዥገሮች ናቸው። የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲያገለግሉ ገንዘብ አስፈላጊ ቢሆንም አገልግሎት የገቢ ምንጭ ወይም የገንዘብ መሥሪያ ብቻ ሲሆን ብልሽት ከአገልግሎት ጀርባ ሳይርቅ እየተከተለ መሆኑ ብዙ ታይቶአል።

3፥ ሰይጣናዊ ሥራ ከጀርባው መኖሩ። ይህ ማለት ሰይጣን የመጀመሪያዎቹን ሁለት ነገሮች ሊጠቀምባቸው አይችልም ማለት አይደለም። የዋህ ስሕተቶችን እንዲሁም ጥቅምን እንደ መሣሪያ እየተጠቀመባቸውም ከአንዳንዶቹ ጀርባ ግን በግልጽ እጁ ይታያል። ከቃሉ ይህን በሰፊው እናገኛለን። ከጴጥሮስ አሳብ በስተኋላ የእርሱ ሥራ ነበረ (ማቴ. 16፥23)፥ አማኞችን ሊያምስና ሊያውክ እጅግ ይወድዳል (ሉቃ. 23፥31-32)፥ በአስቆሮቱ ይሁዳ ክፉ ሥራን ሠርቶአል (ሉቃ. 22፥3-6 እና ዮሐ. 13፥2 እና 27)፥ ቃሉን ያጣምማል (ሉቃ. 4 9-11)፥ የአማኞችን ሥራ፥ የቅዱሳንንም ጉዞ ያደናቅፋል (1ተሰ. 2፥18)፥ ዛሬም ኃይል፥ ሥልጣንና ግዛቶች አሉት (ኤፌ. 2፥2 እና 6፥11-13)፥ የመጨረሻው ዘመን አሠራሩ ደግሞ እጅግ ይከፋል (ራእ. 12፥3-12፥ 13 በሙሉ፥ 20፥3 እና 7-10)። ስለዚህ ከስሕተት ትምህርቶች ጀርባ በግልጽም በስውርም ሰይጣን አይታጣም።

አንዳንዶች የስሕተት ትምህርቶች አስተማሪዎች 'መንፈስ ቅዱስ ተናገረን፥ ጌታ እንዲህ አለን፥ መልአክ ተገልጦ እንዲህ አሳየን...' እያሉ የሚናገሩአቸው ነገሮች በቀጥታ ከቃሉ ጋር የሚጋጩ ነገሮች ናቸው። አንዳንዴም ከቃሉ ጋር የሚመሳሰል ወይም የሚቀራረብ ሐረግን ለመሸፈኛና ለማወናበጃ ይጠቀሙበታል። 'ስሕተት ብዙውን ጊዜ እውነት ባሚባል ፈረስ ጀርባ ላይ ይጋልባል' የሚባል ብሂል አለ። የጌታ መንፈስ ወይም የጌታ መልአክ ከጌታ ቃል ጋር የሚጋጩና የማይስማሙ ነገሮችን አይናገሩምና እንዲህ ያሉትን ትምህርቶችና ትንቢቶች ምንጭ በጸሎት ታግዞ መመርመሩ ተገቢ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች በቀላሉና በየዋህነት የሚከተሉአቸውን መሪዎች ብቻ እንጂ ከእነርሱ ጀርባ ያለውን ባለማስተዋል ነው። 'ውሻ ጌታውን እንጂ የጌታውን ጌታ አያውቅም' ይኋል ይህ ነው። የሚታኘክ ነገር ብቻ የሚሰጡንን ሰዎች ብቻ ከመመልከት አልፈን ከጀርባ ያለውንም መጋረጃ በጸሎትና በቃሉ በመመርመር፥ በእውነትና በፍቅር በመጋፈጥም እንግለጠው። እንግዲህ ስሕተቶች ስናጤን ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ነጥቦች እናስተውል።

የመነቃቃትና ተሃድሶ ንቅናቄዎች በአንድ መልኩ አብያተ ክርስቲያናትን የማዋሃድ ሚና የሚጫወት ተልእኮ እንዳላቸው ይመስላል። በአንድ የካሪዝማዊ ካቶሊኮች ጉባዔ ላይ የሮማው ጳጳስ ይህ አዲስ ንቅናቄ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን የማዋሃድ *(ecumenical)* ንቅናቄ አካል እንደሆነ አጽድቆ ተናግሮ ነበር። አንድ የሚያደርግ ንጥረ ነገሩ ከላይ እንደተጠቀሰው ልምምዳዊነቱ ብቻ ነው። ልምምዳዊነት ደግሞ በትምህርት ባልበሰሉ አጥቢያዎች ሁሉ በቀላሉ ሊከሰት የመቻል ባህርይ አለው። ስለዚህ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች በሰፊው ጴንጤቆስጣዊ ወይም ካሪዝማዊ የሆኑትን ያህል አንዳንድ አማኞች እንደዚያ ባልሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሆነውም የልምምዱ ገበያተኞችና ደንበኞች ይሆናሉ። በዚህም ጴንጤቆስጣዊና ካሪዝማዊ ባልሆኑ አጥቢያዎች እያሉ ከንቅናቄው ጋር የመመሳሰል ባህርይ ይታይባቸዋል። ይህ መመሳሰል እንጂ አንድነት አይደለም። እውነቱ እንዲያውም ካሪዝማዊ ንቅናቄ አንድ አድራጊ ለመሆን የሚጥረውን ያህል በባህርዩ ከፋፋይም ነው። የካሪዝማዊ ክርስትናን ታሪክ ከመሠረቱ አንስተን ስናጠና ንቅናቄው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚጫወተው የአዳሽና የጠጋኝነት ሚና ሳይሆን ያለመርካትን ፈጥሮ ሌላ ማኅበር መሥርቶ መውጣትን ነው። በብዙ አገሮች ውስጥ እጅግ የበዙ ቤተ እምነቶች *(denominations)* የወጡት ከዚህ ንቅናቄ ወዲህና በንቅናቄውም ምክንያት ነው። በእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ላይ ጽኑ አቋም ካላቸው ቤተ እምነቶች ይልቅ አዲስ ቡድን መሥርቶ የመውጣቱ ብዛት የሚታየው ከንቅናቄው ጋር በተቆራኙት ዘንድ ነው። በአንዳንድ ጊዜና ቦታዎች መከፋፈሉና መባዛቱ ልክ እንደ ሴል ክፍፍል እስኪመስል ድረስ እጅግ ነው።

ልምምዱ መሠረታዊ የአስተምህሮ እድገት ፈር ቀዳጅ አይደለም። ከስሕተት ልምምዶችና ትምህርቶች እንድንጠበቅ የሚረዱን ደግሞ መሠረታዊ አስተምህሮዎች ናቸው። ለምሳሌ፥ ብዙ ካሪዝማዊ ካቶሊኮች ይህ ካሪዝማዊነታቸው እንዲያውም ማርያምን ይበልጥ በትጋት እንዲያመልኩ እንደረዳቸው ያወሳሉ። እንግዲህ አንድነቱ በማዕከላዊው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ሳይሆን በልምምዱ ብቻ መሆኑ በዚህ ይታያል።

# የበጎች በግነት

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ የብሂሎች ስብስብ መጽሐፍ እንዲህ የሚል ቃል አነበብሁ፤ "ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን ለከፍተኛ አደጋ እያጋለጠ ያለው ከተኩላዎች ተኩላነት ይልቅ የበጎቹ በግነት





ነው" ይላል፤[8] እውነት ነው። ከተንኮለኞች ተንኮልና ከስሕተተኞች አሠራር ግርግር ይልቅ የምዕመናን በቀላሉ ማመንና እንደዘበት እየተጎተቱ መወሰድ ይብሳል። በቀላሉ አማኝ በሆኑት ዘንድ በዚህ ማመን ላይ የማስፈራራትም ሆነ የማባበል ግፊት ወይም ጉተታ ሲታከልበት ደግሞ መወሰዱ ያለብዙ ችግር ይሆናል።

ለምሳሌ አንድ ሰው ከሕመም እንዲፈወስ ተጸልዮለት በውስጡ በሽታው እንዳለ እያወቀው፥ 'ሕመምህን እንደሌለ ቁጠረው፥ ተፈውሰሃል፥ ይህ የበሽታው ጥላ ነው እንጂ የበሽታው አካል የለም' ቢባል ይህ ሰው ስሜቱንም፥ አእምሮውንም፥ አካላዊ ምልክቱንም፥ ጠቅላላ እውነታውን ሁሉ እርግፍ አድርጎ ቢክድ፥ ይህ ከሞኝነት የከፋ ጅልነት አይደለም? ይህ 'ተፈወስክ' የተባለ ሰው እንዳልተፈወሰ ለማወቅ ምንም ነገር ማድረግ የለበትም። ሰውነቱን ብቻ መስማቱ በቂው ነው። የተፈጥሮ ወይም የደመ ነፍስ መረዳቱ ብቻ እንኳ ያለመፈወሱን ያረጋግጥለታል። ፈውስን የዘመናችን አንዳንድ አስተማሪዎች ሆን ብለው ወይም ባለማስተዋል ውል እንደሌለው ልቃቂት ያወሳስቡታል እንጂ ፈውስ ጥርት ያለ ግልጽ ነገር ነው። ለተፈዋሹም ለተመልካቹም ገሃድ እንጂ ፈውስ ሽፍንፍንና ውስብስብ አይደለም። እንዲህ የመሰሉ በርካታ ምሳሌዎችን መናገር ይቻላል። የሚነገሩንንና የሚታወቁልንን አላስፈላጊ ነገሮች ለመናቅና ላለመቀበል ብቻ ሳይሆን ትክክል አለመሆናቸውን ልቡናችን ከተረዳው ለመፋለምም መቆፍጠን ይኖርብናል።

ሰይጣን ከሩጫችን ሊያስታጉለን ወይም ሊያንቀረፍፈን የሚያሳዝለን ብዙ ነገሮች አሉት። እኒህ ነገሮች የሚስቡ ቢመስሉንም የኋላ ኋላ ወጥመድ መሆናቸው የማይቀር ነው። ጥንት አርካዲያ በሚባል አገር ሾሄኖስ የሚባል ንጉሥ ነበረ። አትላንታ የምትባል አንዲት ውብ ልጅም ነበረችው። አትላንታን እጅግ ብዙዎች ሊያገቡአት ቢመኙም፥ ቢጠይቋትም በእንቢታ ቆየች። የጠያቂዎች ልመና ሲበዛባት አንድ ጠንካራ ፈተና አዘጋጀች፤ ያም በሩጫ እርስዋን ተወዳድሮ የሚያሸንፋትን ሰው እንደምታገባ ለአባቷ ነግራ አሳወጀች። አትላንታ በሩጫ እጅግ ፈጣን ነበረችና የሞከሩት ሁሉ እየተሸነፉ ወጡ። ብዙዎችም የጋብቻ ጥያቄአቸውን ለመጣል ተገደዱ።

ሂፖሜነስ የተባለ አንድ ወጣት ግን የሩጫ ዝግጅቱን ጀመረ። በሩጫ ብቻ ሊረታት እንደማይችል አውቆ ሌላ ዘዴ መዘየድ እንዳለበትም ተረድቶአል። የውድድሩ ቀን ከተቆረጠ በኋላ በዕለቱ የዘመኑ ሯጮች የሚለብሱትን አጭር ቀሚስ ለብሶ መቀነቱን በወገቡ ሸብ አድርጎ ሩጫውን ጀመረ። ሂፖሜነስ ሦስት ከበድ

---

[8] Rosell, p.326.

ከበድ ያሉ ድብልብል ወርቆች ወይም የወርቅ ቡችሎች በመቀነቱ አስሮ ነበር። ከመነሻውም ፈጠነና ቀድሞአት ይሮጥ ጀመር። አትላንታም እንደማያሸንፋት በሚተማመን ሁኔታ እመር እያለች ከኋላው መሮጥ ቀጠለች። የሩጫውን ርቀት ግማሽ እንደሮጡ አንዱን የወርቅ እንክብል ጣለው። አትላንታም ወርቁ የወደቀበት ስፍራ ስትደርስ አየችው፤ የንጉሥ ልጅም ብትሆን ከሴትነት ደመ ነፍሷ የተነሣ ትታው መሄድ አልፈለገችም፤ አነሣችና ያዘችው። ከጥቂት መቶ ሜትር ርቀት በኋላ ከቀሩት ሁለት አንዱን ጣለ። አሁንም አትላንታ አንሥታ በራስዋ መቀነት አስገባችው። አሁን ሂፖሜነስ እየቀለለው እርስዋ እየከበዳት ሩጫቸውን ቀጠሉ። እርሱ እየፈጠነ እርስዋም እየተንቀረፈፈች ሲሮጡ በመጨረሻም የቀረውን አንድ ጣለላት፤ ይህኛውንም አልማረችውም አንስታ በመቀነቷ ዶለችው። በመጨረሻም አትላንታ ተሸነፈችና ሂፖሜነስ ሚስቱ አድርጎ ወሰዳት።

ደመኞችን በክርስትና መንገዳችን ላይ ጉዞአችንን የሚያከብዱብንን ልናልፋቸው እንዳንችል የሚያዳጉንን ከዘላለማዊ ጉዞአችን አንፃር ስናያቸው ግን እንደ ምናምንቴ ሊቆጠሩ የሚገባቸውን ነገሮች ከፊታችን እየጣለና እያስነገተን ኋላ ሊያስቀረን ይሻል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ በጎች ሲናገር በአእምሮአችን መሳል ያለብን በእስራኤል ወይም በመካከለኛው ምሥራቅ ያሉትን በጎች ሁኔታ ነው። በኛ አካባቢ ከተለመደው የበግ ሁኔታ በመጠኑ ይለያሉ፤ በዚያ አካባቢ የሚረቡት በጎች ጥንት ለመስዋዕት ካልሆነ በቀር ከእርድ ይልቅ በአብዛኛው ለጠጉራቸው ጥቅም ነው የሚረቡት። ደግሞም፥ እረኛቸው ከኋላ ሆኖ ከመንዳት ይልቅ ከፊት ሆኖ ነው የሚጠራቸው። ሆኖም በየትም የሚገኙ በጎች የሚመሳሰሉባቸው ባህርያት አሉ። በጎች በተፈጥሮ ሞኞች ናቸው፤ የአቅጣጫ ስሜት የሌላቸውና መሪ ወይም ጠባቂ ካልኖራቸው በቀር የሚቅበዘበዙና በቀላሉም የሚጠፉ እንስሳት ናቸው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ስለሆኑ ነው ኢሳይያስ በምዕ. 53፥6 ላይ፥ 'እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፥ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ' ያለው።

በጎች የማይገሩ፥ የማይሰለጥኑ፥ ራሳቸውን የማይከላከሉ፥ የሚበረግጉ፥ ከእረኛቸው ከራቁ ወይም ድምጹን ካልሰሙ በቀላሉና ባለማስተዋል ለአደጋና ለሞት የሚዳረጉ ፍጡራን ናቸው። በአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች በበጎችም ተመስለናል። እንዲህ ከሆነ ከስሕተትና ከአደጋ ለመጠበቅ ማድረግ ያለብን ትልቅ ነገር የእረኛችንን ድምጹን መስማት፥ ማለትም ቃሉን ማጥናት እና እረኛችንን በቅርብ መከተል ነው። በዚህ ዘመን የእረኛችን ቃል በየጊዜው በድምጽ የምንሰማው ሳይሆን የምናነብበው ቃሉ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር እረኞች እንዲሆኑን የሰጠን ሰዎችም አሉን። ከሁሉ በላይ የሆነ እረኛችን ደግሞ ክርስቶስ





ነው፤ ዮሐ. 10፥1-10፤ ዕብ. 13፥20፤ 1ጴጥ. 5፥2-5። ቃሉን እየመረመሩ እነርሱን መስማት ጥበብ ነው።

አንዳንድ የስሕተት ትምህርቶችን ስናስብ አስተማሪና ጀማሪዎቹን ብቻ ከማውገዝ አልፈን ማየት መቻልም አለብን። ተከታዮችን የሚያስተው መሪ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ የተገላቢጦሽ ተከታዮችም መሪን ሊያሳስቱ ይችላሉ። እርሱ መጀመሪያ ከመስመር ሲወጣ ተከታዮቹ አስተውለው አብረውት ካልወጡ ተመልክቶ ወደነበረበት ወደ መስመሩ ይገባል። አንዳንድ ተከታዮች መሪው የሄደበትን ፍለጋ ብቻ እያዩ ይከተላሉ። አንዳንዶች መሪውን ብቻ ያያሉ። አስተዋዮች ግን እርሱን ብቻ ሳይሆን የሚሄድበትንም አቅጣጫ አማትረው ያያሉ። እርሱ ራሱ ትልቁን መሪ፥ የእረኞችን አለቃ ይከተል አይከተል እንደሆነ ያስተውላሉ። ሞቅታ ፈላጊ ተከታዮች ብዙውን ጊዜ አሳሳች ተከታዮች ናቸው። ለምሳሌ፥ አንድ ሰው በአንድ ጉባዔ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያስቀመጠውን እውነት ወይም ትንቢት ቢናገር የተነገረውን ነገር ከቃሉ አንፃር መመርመር የጉባኤው ፈንታ ነው። ነገር ግን፥ ያንን የተናገረውን ሰው ሌላ ጊዜም እንዲናገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መገፋፋት፥ 'እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር፥ ስለዚያ ነገር፥ ስለ እገሌ፥ ስለ እገሊት፥ ስለዚህ ዓመት፥ ስለሚመጣው. . . ምን አለ?' በማለት መወጠር ያልተባለውን 'እንዲህ ይላል እግዚአብሔር' እንዲል መጭመቅና መፈታተን ነው። ከዚህ የተነሣ የጥንቆላ ሥራ የሚመስሉ ነገሮችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቶአል። ሰዎች ውሸትን ከለመዱ እውነት አያረካቸውም። ሰዎች ለራሳቸው የሚመቹአቸውን አስተማሪዎች የሚያከማቹበት ዘመን ላይ መሆናችንንም መዘንጋት የለብንም፤ 2ጢሞ. 4፥3-5። በጭፍን መከተልና የአሳቾች ሰለባ መሆን የራስ ጉዳት ብቻ ሳይሆን ለእነርሱም የሚቀጥለውን ምዕራፍ የሚሄዱበት ጉልበት መስጠት ወይም ቲኬት መግዛት ነው።

በቅርብ የማውቃት አንዲት እህት (ተመ) ክርስቲያን ከሆነች ጥቂት ዓመታት ያስቆጠረች ወጣት ናት። ተመ ከአማካይ ወጣቶች ይልቅ ስሜታዊም ናት። ወደነበረችበት ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰባኪ ተጠርቶ መጥቶ ስለ ብልጽግና ሰበከ። ሰባኪው በመጨረሻ እንዲበለጽጉ ቢፈልጉ ምዕመናኑ ያላቸውን መስጠት እንዳለባቸው አስረዳ። በመባ መስጠት ጊዜ ምዕመናን እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ልማድ እየተነሡ ወደ ፊት በመሄድ መስጠት ጀመሩ። ተመ በቦርሳዋ ውስጥ ከነበረው 300 ዶላር አንድ መቶውን አውጥታ ሰጠች። የሰዎቹ ስጦታ ያላረካው ሰባኪ ከመባው በኋላ እንደገና ስብከቱን ቀጠለ። 'እግዚአብሔር የሰጣችሁትን ሳይሆን በኪሳችሁና በቦርሳችሁ ውስጥ ያስቀራችሁትን ነው የሚያየው' እያለ በማስፈራራት ተናገረ። ቢሰጡ እግዚአብሔር እንደሚባርካቸው እንደሚጠነቀቅላቸው፥ ባይሰጡ ግን መርገም ይዘው እንደሚመለሱ

እየተነተነ ተናገረ። ለእግዚአብሔር ያለመስጠት፥ 'እኔ ለራሴ እጠነቀቃለሁ፥ አንተ አትጠንቀቅልኝ ማለት ነው፤ እግዚአብሔር እንዳይጠነቀቅላችሁ ከፈለጋችሁ ገንዘባችሁን ለራሳችሁ አስቀሩ' አለ። እንደገናም ሰዎች እንዲሰጡ ጋበዘ። እንደገናም ሰዎች እየተነሡ ሰጡ። ተመ በቦርሳዋ የቀራትን ገንዘብ ሳንቲሞችም ሳይቀሩ በሙሉ አራግፋ ሰጠች። በስሜት ገፋፊነትና በየዋህነት። አምልኮ ካለቀ በኋላ ወደቤትዋ መመለስ አለባት። የሚያደርሳት ሰው የላትም፤ ታክሲ መጥራትም አውቶቡስ መያዝም አትችልም፤ አሁን ገንዘብ የላትም። ሌላው ቀርቶ ሰዎች ለመጠየቅ ስልክ የምትደውልበት ሳንቲም እንኳን አልነበራትም። ጊዜውም መሽቶአል። በጨለማና በአገሩ ከዜሮ ዶግሪ በታች በሆነ ኃይለኛ ብርድ ረጅም መንገድ ከቤተ ክርስቲያን እቤቷ ድረስ በእግር መኳተን ኖረባት።

ተመ ይህን ስሕተቷን አላስተዋለችም። ከዚህ በሚያኮማትር ብርድ ከተንከራተተችበት ጊዜ ብዙም ሳይቆይ ደግሞ በሆድዋ ውስጥ አንድ ሕመም ተሰማት። ወደ ሐኪሟ ዘንድ ሄዳ ካዋየች በኋላ ሆስፒታል ሄዳ ራጅ ተነሣች፤ ሌላም ምርመራ ተደረገላት። ውጤቱን ተመልክቶ ሐኪሟ ሆድዋ ውስጥ አንድ ዕጢ መኖሩን ነገራትና ቶሎ መውጣት እንዳለበትም አስረዳት። እንዲጸለይላት ተናገረችና ተጸለየላት። የጸለየላት እናመልክባት የነበረች ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌም እንደተፈወሰች ነገራት። እንደተፈወሰች ሳትፈራ እንድታውጅና እንዳትጠራጠርም አስጠነቀቃት። ተፈውሻለሁ ብላ በጉባኤ መሰከረች፤ የሕክምናውን ቀጠሮም ሰረዘች። የሕመሙን ስቃይ ግን በስውር እየቻለችው እንጂ እየበረታባት መጥቶአል። ሲያቅታት ከብዙ ወራት በኋላ ወደ ሐኪምዋ ዘንድ ስትሄድ እንደገና ራጅ አስነሣትና ሲያየው ከበፊቱ መጠን 80 በመቶ ጨምሮአል። በአንድ ቦታ ተከማችቶ ወደ ውስጥ እያደገና እያበጠ መካከለኛ ኳስ አህሎአል። አሁን ግን ከ6 ወራት በፊት ቀዶ ጥገና ሊደረግላት እንደማይችልም ነገራት። በዚያ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ዕጢውም ሕመሙም እያደገ ነው። በመጨረሻ ሕክምናው በሚደረግበት ጊዜ ወደ ስምንት ኢንች ወይም ሃያ ሳንቲ ሜትር ርዝመት ያለው ቦታ ተቀድዳ ከአንድ ኪሎ በላይ የመዘነ ትልቅ ዕጢ ነበር ከውስጥዋ የወጣው። ተመ በእንደዚያ ያለ ልምምድ ውስጥ መሆንዋ ስሕተት መሆኑን ፈጥና አልተረዳችም። እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ሳለ የውሸት ፈውስን ግን የማይቸር አምላክ መሆኑ ቢነገራትም አልተቀበለችም። ስለዚህ እነዚህንና ሌሎችም ብዙ አላስፈላጊ ዋጋዎችን ከፈለች። የአካል ብቻ ሳይሆን የስሜት፥ የአእምሮ፥ የገንዘብ፥ የመንፈስም ኪሳራ ደረሰባት። ብዙዎቻችን እንዲህ ያሉ ጥቂት የዋኅ ጓደኞች አናጣም። ታዲያ ጉዳታቸው አያሳዝነንም?





# የተኩላዎች ተኩላነት

ከበጎች በግነት ያላነሰ የስሕተት ትምህርቶችንና ልምምዶችን የሚያስፋፋው የተኩላዎች ተኩላነት ነው። በመሪ በጭፍን መነዳት ከዘመናዊዎቹ የመነቃቃትና ተሃድሶ እንቅስቃሴዎች ጉልህ መለያዎች አንዱ ነው። በዚህ እንቅስቃሴ አካባቢ በሌሎቹ ዘንድ እንደሚታየው ሁሉ መሪዎችን በተመለከተ ተቀባይነት ያገኙ ስሕተቶች አሉ። እንደማይሳሳቱ መገመት፥ እንደማይደርቁ ሆነው እንደተቀቡ መቀበል፥ የሚሉትን ያለጥርጥር መቀበል፥ ያለመጠየቅ፥ ሲያጠፉ ዝም ማለት፥ ያለ እነርሱ ምንም እንደማይቻል ማሰብ፥ ዐይን ጨፍኖ የረገጡበት መርገጥና ወደ ሄዱበት መሄድ ጥቂቶቹ ናቸው። የሚቸሩልን ዋሾ ተስፋዎች ማዘና ጊያና የተከበሩ ነገሮቻችን ተዘርፎ መወሰጃ ሊሆኑ እንደሚችሉም እንወቅ። አንድ ጊዜ በኒው ዮርክ ለሚኖሩ ባልና ሚስት ለብሮድዌይ የሙዚቃ ዝግጅት መግቢያ ቲኬት ተገዝቶ ተላከላቸው። ብሮድዌይ በኒው ዮርክ የሚገኝ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀ የኪነ ጥበባት ማዕከል ነውና ወደዚያ መሄድ ለብዙዎች እንደ ትልቅ ዕድል ይቆጠራል። እነዚህ ባልና ሚስትም ማን እንደላከላቸው ባላወቁት ቲኬት በዝግጅቱ ቀን ይሄዳሉ። በትዕይንቱ በጣም ተደስተውና ረክተው ያላወቁትን ጋባዥ በልባቸው አመስግነው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ወደ አፓርታማቸው ሲደርሱ በሩ ክፍት ነው፤ የጌጣ ጌጥ ሙዳዮችና ውድ የሆኑ ንብረቶቻቸው በሙሉ የሉም፤ መኝታ ቤታቸው ሳይቀር ተበርብሮአል፤ በአንዱ ትራስ ላይ ብቻ የተጻፈ ማስታወሻ አለ፤ የተጻፈበትም፥ 'አሁን ማን እንደጋበዛችሁ አውቃችኋል' የሚል ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚነሡ ራሳቸውን በገዛ እጃቸው የቀቡ መሪዎች ከራሳቸው መሰሪነት ወይም ከተከታዮች ጅልነት እንዲሁም ከሰይጣን የረቀቀ አሠራር የተነሣ ተቀባይ አግኝተው ሰዎችን ወደ አካላዊ፥ አእምሮአዊ፥ ስሜታዊ፥ መንፈሳዊ፥ ጉስቁልናና ድኅነት፥ ወደ ማጥና ወደ ገደል ሲመሩ ኖረዋል። አንዳንዶች ካሉበት ከፍተኛ ስፍራና ለራሳቸው ከሰጡት ወይም ከተሰጣቸው ከፍተኛ ግምት የተነሣ ወደ መንፈሳዊ ዕውርነት ይገባሉ። በዙሪያቸው ያለውን ጥፋትም ማየት ይሳናቸዋል። ሰዎችን በመንፈስም፥ በአእምሮም፥ በገንዘብም፥ በማኅበራዊ ተዛምዶም ሲያጎሳቁሉ ብቻ አይደለም፤ በአካልም ሲገድሉ አያስተውሉም። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆንልን ጂም ጆንስ የተባለው ሰውና በፈረንጆች አቆጣጠር በ1978 የፈጸመውና ዓለምን ያስደነገጠው ታሪክ ነው።

ፒፕልስ ቴምፕል በሚል ስያሜ የሚታወቀው ጉባኤ የተጀመረው በአሜሪካዊው ጄምስ ወይም ጂም ዎረን ጆንስ እኤአ በ1953 ነው። በዚህ ጊዜ ጂም ገና የ21 ዓመት ወጣት ነበር። በሚዙሪ ግዛት በእስፕሪንግፊልድ ከተማ በሚገኝ አንድ ጴንጤቆስጣዊ ኮሌጅ ውስጥም ተምሮአል። ሆኖም ከዚህ ኮሌጅ የተማረው ቁም ነገር ቢኖርም በአገልግሎት ዘመኑ ውስጥ የጠፋበት ይመስላል። እንደ ብዙዎች የስሕተት ልምምዶች ሁሉ ሲጀምር ጤናማ የክርስትና አነሣስ ነበረው። አገልግሎቱን የጀመረውም ኢንዲያናፖሊስ በምትባል ከተማ ሲሆን በዚያ ተቀባይነትን አላጣም። በኢንዲያና ግዛት ውስጥ የተጀመረው ይህ ንቅናቄ በመጀመሪያ ዓመታቱ በፍጥነት ሊያድግ የቻለው በሁለት ምክንያቶች ነው። እኒህም የጂም የስብከት ችሎታውና ለከተማዋ ድሆች ያሳይ የነበረው አሳቢነቱ ነበሩ። ጉባኤው በመጀመሪያ ጥቁሮች የበዙበት ሆኖ በፍጥነት አደገ። ሆኖም፥ ከዕድገቱ የተነሣ ሳይሆን ከፈጠራቸው ማኅበራዊ፥ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ችግሮች የተነሣ ወደ ካሊፎርኒያ ለመዛወር ተገደደ። በተለይ ይደረጉ የነበሩት የውሸት ፈውሶች ሰዎችን በጣም ማበሳጨት ጀምረው ነበር። ፒፕልስ ቴምፕል መጀመሪያ በ1965 ወደ ዩኪያ፥ ቀጥሎ ደግሞ በ1971 ወደ ሳን ፍራንሲስኮ ተዛወረ።

የጂም አገልግሎት የተቀረጸው ከድንኳን መነቃቂያ ስብሰባዎች ልምምድ፥ ከማንም ቤተ እምነት ጋር ካልወገኑ ነጻ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ባለ ግንኙነት፥ ከካሪዝማዊና ከአርነት ወይም ዴሊቨረንስ ንቅናቄዎች፥ ከካቶሊካዊ ሥርዓተ ሃይማኖት፥ ከጴንጤቆስጣዊ ግብታዊነት፥ ከማርክሳዊ ሶሻሊዝም፥ ከምሥራቃውያን ሃይማኖቶች፥ በተለይም ደግሞ ደጋግሞ ከመወለድ፥ ከብልጽግና ተስፋ፥ እንዲሁም ከአካላዊ ፈውስ ከተወሰዱ ትምህርቶች ድርና ማግ ነው። በሐዋርያት ሥራ ከምትገኘው ከመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ከረጅም ጊዜ የማርክሲዝም አድናቂነቱና ኮሚኒስታዊ አመለካከት የቀረጸው 'ሐዋርያዊ ሶሻሊዝም' ብሎ የሰየመው ተሰባስቦ የመኖር ድንጋጌም አለው። ጂም ስለራሱ እጅግ የገዘፈ አመለካከት ያለው ሰው ነበር። ምናልባት ለማኅበሩ ኋለኛ ጉዳት መጥፎ ጥላ ካጠሉት ነገሮች ይህም ይገኝበታል። ከማንም አስበልጦ ራሱን በማየት በአስፈላጊነቱና በጠቃሚነቱ አሳብ የሰከረ ሰው ነበረ። ስሕተቱን የጀመረውም ከዚህ በመንደርደር ነበር። መጀመሪያ የክርስቶስን አምላክነትና የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን ክዶ ራሱን የማኅበሩ የመጨረሻው ባለ ሥልጣን እንዲሁም መሢሕ አደረገ። መጽሐፍ ቅዱሱን እየወረወረ፥ 'ይህን ሳይሆን እኔን ስሙ' ማለት ጀመረ። የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ምንም በትሕትና የታጀቡ ቢሆኑም የኋለኞቹ ግን በተቆጣጣሪነትና በሥልጣን፥ በኩራትና በእብሪት ጥም የተሞላባቸው ነበሩ። የእርሱን መንገድ የሚቃወም ሰውና አሳብ በአካባቢው እንዲኖር አይፈልግም። አምፌታሚን የሚባል





አነቃቂ መድኃኒት በመውሰድ ውሸታም 'የእምነት ፈውሶች' በብዛት ማካሄድ ጀመረ።

ጥቂት በጥቂትም በማኅበሩ ውስጥ የሚደረጉት ከቤተ ክርስቲያን አካባቢ የማይጠበቁ ነገሮች መሹለክና በውጭ ላሉት፥ በተለይም ለመገናኛ ብዙኃን መሰማት ጀመሩ። ድብደባዎች፥ የማስገደድና የማዋረድ ድርጊቶች፥ የገንዘብ ምዝበራና ብክነት፥ እንዲሁም ጂም ከአባላቱ በአንዳንዱ ላይ የሚያንጸባርቀው ድንበር የለሽ ወሲባዊ ፍላጎት አካባቢውን ለቅቆ እንዲሄድ አስገደደው። በተለይ በስተኋላም በጋዜጦች ላይ በስፋት መጻፍ የጀመሩትን ቅሌቶች ሊቋቋማቸው አልቻለምና ስለመሰደድ ማስተማር ጀመረ።

ጂም በ1977 በዚህና በሶሻሊስታዊ አመለካከቱ በመገፋፋት በጉያና (ደቡብ አሜሪካ) ውስጥ ትልቅ የእርሻ ቦታ በመመራት በግብርና ላይ የተሰማራ ማኅበር መሥርቶ አገልግሎቱንና የጉባዔውን አባላት ሁሉ ከአሜሪካ ወደ ጉያና አዘዋወረ። የዋኃን ተከታዮቹም አብረውት በመሄድ ይህን አዲስ መንደር በመሪያቸው ስም ጆንስታውን ብለው ጠሩት። ይህ በአንዳንዶች ዘንድ በራስ ላይ እንዳመጡት ስደት ብቻ ሳይሆን እንደ ግዞት የተቆጠረ እርምጃም ነበረ። ቄስ ጂም 'መላእክት' ብሎ የሰየማቸው የግል ጠባቂ ታጣቂ ወታደሮች ጓድም ነበረው። ደንብ የሚጥሱ አባላት በነዚህ መላእክት እንደጥፋታቸው መጠን ይቀጣሉ። የጂም ማኅበር ከሃይማኖታዊ ማኅበር ወደ ገበሬዎች ወይም አምራቾች ማኅበር የተቀየረ መሰለ። ለረጃጅም ሰዓቶች የጉልበት ሥራ ማሠራት፥ ማስፈራራት፥ ስም ማጥፋትና መወንጀል፥ የዱላ ድብደባ፥ እንዲሁም 'የማሻር ክፍለ ጊዜ' ተብሉ የተሰየመ የተለያዩ ዓይነት ቅጣቶች የሚፈጸሙበት ቅጣት ተጀመረ። ለመጀመሪያ ጊዜ ግድያም ተፈጸመ። እዚያ የሚኖሩት አባላት ሁሉ መውጣትም ሆነ በሌላ ቦታ መንቀሳቀስ ወይም ወዳገራቸው መመለስ እንዳይችሉ ፓስፖርቶቻቸው ተወስዶ በጂም ቢሮ ተቆለፈበት።

ፒፕልስ ቴምፕል ተብሎ በካሊፎርኒያ በቄስ ጂም የተጀመረው ይህ የስሕተት ሃይማኖት በኅዳር ወር 1978 በጉያና ውስጥ የዓለምን ሕዝብ ያስደነገጠና ለስሕተት ሃይማኖቶች ያለውን አመለካከት በእጅጉ የቀየረ ነገር ፈጸመ። ከዋናው ነገር መከሰት በፊት ኅዳር 14 ቀን የካሊፎርኒያ ምክር ቤት አባል የሆነ ሊዮ ራየን የተባለ ሰው የስሕተት ትምህርቱ ተከታዮች ዘመዶች ከሆኑ ሰዎች ጋር በመሆን ለምርመራና ለማጣራት ሥራ ወደ ጆንስታውን ሄደ። ከእርሱ ጋር ወደ አሜሪካ ሊመለሱ የሚወዱ ቢኖሩ ይዞአቸው እንደሚመጣ ቃል ገብቶ ነበር። ምርመራውን አጠናቅቆ ኅዳር 18 ቀን አብረውት ከመጡት ሰዎች ሌላ በፈቃዳቸው ለመመለስ የወሰኑ 14 የጂም ተከታዮች ተጨምረው ሁሉም ወደ አውሮፕላናቸው ማምራት ጀመሩ። እንደሚጋለጥ በመፍራት ራየንና አብረውት ያሉት ሰዎች በሙሉ እንዲገደሉ ጂም ትእዛዝ ሰጠ።

ወደ አውሮፕላናቸውም ከመግባታቸው በፊት ራየን፥ ሦስት ጋዜጠኞችና አንድ የጂም ተከታይ የነበረ ሰው በጥይት ተገደሉ።

ያመለጡት ሰዎች ሌሎች ባለሥልጣኖችን ይዘው ተመልሰው እንደሚመጡ በመረዳት ጂም 'ነጭ ምሽት' የተባለውን በጥንቃቄ የተሰላ የአምልኮ መርሀ ግብር መምራት ጀመረ። መርሐ ግብሩ ግን አምልኮ ሳይሆን የጅምላ ግድያ ዝግጅት ነበረ። ከተደረጉት ነገሮች አንዱ ኩል ኤድ የሚባል ለስላሳ መጠጥ መጠጣት ነው። መጠጡ ግን ሳያናይድ በተባለ መርዘኛ መድኃኒት የተበጠበጠ ነበረ። ወታደሮችና መርማሪዎች ወደቦታው የመጡት በማግሥቱ ነው። በቀደመው ቀን አምስት ሰዎች ስለተገደሉ ጠንካራ ሠራዊት ነው በከፍተኛ ጥንቃቄ የመጣው። በጣም እስኪጠጉ ድረስ ምንም የተከፈተባቸው ተኩስ አልነበረም። ቅጥሩን ጥሰው ሲገቡም ሁሉም ነገር ጸጥ ያለ ነበር። የጉያና ወታደሮች ወደ መሰብሰቢያው ዳስ ዘልቀው ሲገቡ ያዩት ግን እጅግ ዘግናኝ ትዕይንት ነበር። ሜዳው በሙሉ በ913 ሰዎች ሬሳ ተሞልቶ ነበር። ጥቂቶቹ በጥይት ተመትተው፥ የተቀሩት በሙሉ ግን ሳያናይድ በገባበት መጠጥ ነበር የሞቱት። የ47 ዓመቱ ቄስ ጂም ጆንስም ጭንቅላቱ በጥይት ተመትቶ ወድቋል።

የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ምን ይመስሉ እንደነበር እዚያ ከነበሩትና ከተረፉት በአንዱ የቀረበው ዘገባ እንዲህ ይላል፥

> ጆንስ በድምጽ ማጉያው ስለሞት ውበትና ሁሉም ከሞት በኋላ እንደገና እንደሚገናኙ እየተናገረ ሳለ ብዙዎቹ መቶዎች የትምህርቱ ተከታዮች ወደ መሰብሰቢያው ዳስ መግባት ጀመሩ። መሣሪያ በታጠቁ ዘበኞች ተከበው ሳሉ ሳያናይድ የተደባለቀበት ኩል ኤድ የያዙት ዕቃዎች እየመጡ ተቀመጡ። ብዙዎቹ በፈቃደኝነት ሲጠጡ ሌሎቹ በግዴታ እንዲጠጡት ተደረጉ።
>
> መጠጡ የተጀመረው በሕፃናት ነበር፤ ቢያንስ ሰማንያ ሕፃናት ይህን ገዳይ መርዝ እንዲጠጡ ተደርገው ነበር፤ ከዚያም አዋቂዎች መውሰድ ጀመሩ። ለጥቂት ደቂቃዎች ሁሉ ነገር ሰላማዊ ነበር፤ ከዚያ በኋላ ግን ከመርዙ ግፊት የተነሣ የተፈጠረው መንፈራገጥና መንፈራፈር ሲጀመር ሁሉ ነገር ከቁጥጥር ውጪ ሆነ። ሕፃናት በከፍተኛ ድምጽ መጮኽ ጀመሩ፤ በአጠቃላይ እጅግ አሰቃቂ ሁከት ሆነ። እንዲያ ከሆነ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ግን ሁሉም ሞቱ፤ ጸጥታም ሆነ።[9]

ለምን ይህን የመሰለ ዘግናኝ ስሕተት ሊፈጸም ቻለ? ያለምንም ጥርጣሬና ጥያቄ የተሳሳተ መሪን እንዳልተሳሳተ አድርጎ በመቀበልና በመከተል ነው ይህ የሆነው። ይህ ይበልጥ መብራራት የሚችለው የተሳሳተ መሪ የሰዎችን አእምሮ ለመቆጣጠር የሚጠቀምባቸውን ስልቶች ሲመረመሩ ነው። ይህ በኅዳር ወር 78 የተፈጸመው እልቂት ዜና ሰሚዎችን በጥልቅ ቢያስደነግጥም አእምሮን

[9] Galanter, pp. 119-124.





የሚቆጣጠሩና በመሪዎች ላይ የሚያተኩሩ የስሕተት ትምህርቶች ምን ያህል አደገኛ መሆናቸውን መስክሮአል። ጉልህ ማስጠንቀቂያና የማንቂያ ደወልም ሆኖአል። ተኩላዎች የበግ ለምድ ቢለብሱና በግ ቢመስሉም ተኩላዎች ናቸው። ለምዳቸው ብቻ ሳይሆን በሆነ ተአምር ገላቸውም እንኳ በግ ቢሆን ልባቸው ግን ያው የተኩላ ነውና አይለወጥም።

የጂም ጆንስ ማኅበር በጉልህ የታወቀው ከስሕተት ትምህርት ጋር የተያያዘ ፍጅት *(cult mass suicide)* ቢሆንም ነፍሰ ገዳይ የስሕተት ትምህርቶች ከጆንስ ጋር አልሞቱም። ከዚያ ወዲህ ከሆኑት ጉልህና የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት ከሳቡት መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ። ዘገባዎቹን ያገኘሁት ከተለያዩ ጋዜጦችና ድረ ገጾች ሲሆን የመረጥኳቸው ክርስቲያናዊ ጅማሬ ያላቸውን ወይም ክርስቲያናዊ ከልት የሚባሉትን ነው። የቀውሶቹ ዘመናት አቆጣጠር በፈረንጆች ነው።

ኅዳር 1፥ 1986 በምዕራብ ጃፓን ባህር ዳርቻ ራሳቸውን ያቃጠሉ ሰባት ሴቶች ሬሳ ተገኘ። ሴቶቹ ራሳቸውን ለምን እንደገደሉ በተውት የተጻፈ ማስታወሻ ኪዮሃሩ ሚያሞቶ የተባለ መሪያቸው በመሞቱ መሆኑን ጠቅሰዋል። ሴቶቹ የእውነት ወዳጆች ቤተ ክርስቲያን *(Church of the Friends of Truth)* አባላት ነበሩ።

በነሐሴ ወር 1987 ፓርክ ሱን ጃ የተባለችው ኮሪያዊት ቄሲት ደቀ መዛሙርት የሆኑ 32 ሰዎች ሞተው ተገኙ። ፖሊስ እንዳረጋገጠው ከሆነ ከነዚህ ሰዎች አብዛኞቹ የሞቱት ወዲያው የማይገድል መርዝ ጠጥተውና ጉሮሮአቸው በስለት ተቆርጦ ነው።

መጋቢት 19፥ 1993 ከ80 የሚበልጡ የዳዊት ቁጥቋጥ ማኅበር *(Branch Davidian)* አባላት በአሜሪካ በቴክሳስ ግዛት ዌኮ ከተማ ሞቱ። እነዚህ ዴቪድ ኮሬሽ በተባለ ሰው ይመሩ የነበሩ ሰዎች በትልቅ ግቢያቸው ባለ ቤት ውስጥ ለብዙ ሳምንታት ከመንግሥት የጸጥታ ኃይላት ጋር ሲፋጠጡ ከቆዩ በኋላ በ51ኛ ቀናቸው ያሉበት ቤት ተቃጥሎ ሁሉም ሞቱ። በምርመራ በተገኘው ውጤት መሠረት ከሞቱት ሰዎች መካከል ጥቂቱ ከእሳቱ ቀድሞ ጭንቅላታቸው በጥይት እየተመቱ የሞቱ ነበሩ።

መጋቢት 26፥ 1997 በአሜሪካ በካሊፎርኒያ ግዛት ሳን ዲየጎ ከተማ 39 የመንግሥተ ሰማያት ደጅ *(Heaven's Gate)* ማህበር አባላት በቮድካ በተበጠበጠ መርዝ ራሳቸውን ገድለው ተገኙ። እንደነዚህ ሰዎች እምነት በዚያ ዓመት በዓለም ሁሉ ይታይ የነበረው ኮሜት ሄሊ ቦፕ የተባለው ጅራታም ኮከብ ከመሬት ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስደውን የሰማይ መንገድ ቀዳጅ ነውና በአካል ያለዚያም ነፍሳቸው እርሱን ተከትላ ወደ መንግሥተ

ሰማያት እንደምትገባ ያምኑ ነበር። እነዚህ ሰዎች ማኅበራቸው በገዛው ትልቅ ግቢያቸው ውስጥ ከስሕተት ትምህርቱ ጀማሪዎች ከማርሻል አፕልዋይት እና ቦኒ ኔትልስ ጋር በአንድነት ራሳቸውን አጠፉ። በአካል ሊሄዱ የሚችሉበት ግምታዊ እምነት ከጅራታም ኮከብዋ ኋላ በራሪ መንኮራኩር እንዳለች በመቀበል ነበር። ከመሞታቸው በፊት በማኅበራቸው ድረ ገጽ ላይ ባሰፈሩት መልእክት ሞታቸው ከዝቅተኛው ሕይወት ወደ ከፍተኛው ሕይወት ተመርቀው መሄዳቸው መሆኑን ገልጠዋል።

በፈረንጆቹ ቆጠራ ሃያኛው መቶ ሊያልቅ ጥቂት ወራት ሲቀሩት በርካታ ከ2000 ጋር ዓለምም እንደምታልፍ ያምኑ የነበሩ ሺሃውያን የስሕተት ትምህርቶች *(Millennium Cults)* ተፈጥረው ነበር። ቀደም ሲል የነቃ ጥናት በማድረግና ተጠርጣሪ የሆኑትን ሁሉ የእስራኤል ፖሊስ እያፈሰ አስወጣ እንጂ አንዳንዶች ማኅበሮች ከኢየሩሳሌም ለመነጠቅ ወይም ያ ካልሆነ ራሳቸውን በኢየሩሳሌም ለማጥፋት በማሰብ ወደዚያ ሄደው ነበር። ሃያ አንደኛ ምዕት ዓመት ያለ ክርስቶስ መምጣት መግባቱ አንዳንዶቹን ሲያሳፍር ሌሎቹን መሳሳታቸውን አረጋግጦላቸዋል።

በዩጋንዳ ግን ዓመቱም ከገባ በኋላ የዓለም ፍጻሜ መቅረቡን ሲያውጅ የቆየው የእግዚአብሔርን ዐሠርቱን ትእዛዛት የመመለስ ንቅናቄ *(Movement for the Restoration of Ten Commandments of God)* የተባለ ማኅበር ከነአባላቱ ከመጥፋት አልተመለሰም። የዚህ ማኅበር መሪዎች ከሌላ አብያተ ክርስቲያናት የሆኑ ሦስት ቀሳውስት ናቸው። አባላቱ ያላቸውን ሁሉ እየሸጡ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ እንዲዘጋጁ ሲሰበኩ ቆይተዋል። በደቡብ ምዕራብ ዩጋንዳ በካኑንጉ ከተማ ትገኝ የነበረችው የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባላት መጋቢት 18፥ 2000 ለብዙ ሰዓታት በመንጫጫትና በመዘመር ከቆዩ በኋላ ከጆንስታውን እልቂት ወዲህ በሟቾች ቁጥር ሁለተኛ የተባለውን እልቂት ፈጸሙ። እኒህ ያለቁት ቤተ ክርስቲያናቸውን በላያቸው በማቃጠል ሲሆን ቢያንስ 235 ሰዎች ሞተዋል። ይህና የጆንስታውኑ እልቂቶች ለመሞት መምረጥ የማይችሉ ሕፃናትም ስለነበሩባቸው እልቂት ብቻ ሳይሆኑ ግድያም ጭምር ነበሩ። የብዙ ሰዎች የተቃጠለ ሬሳ በበሮችና በመስኮቶች አጠገብ መገኘቱ ቤተ ክርስቲያኑ ሲቃጠል ለመሸሽና ለመውጣት የተደረገውን ትግል ያመለክታል።

እነዚህ ጎልተው የታወቁትና በመገናኛ ብዙኃን ኡ! ኡ! እና ጉድ የተባለባቸው ናቸው። በጥቂት ቁጥሮች እና በብዙ ቦታዎች የሞቱ አያሌ ሊኖሩ እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም። ይህ መድኃኒታቸውን እንዲጥሉ እየተነገራቸው እየጣሉ በሽታቸውን ያባዙትን ወይም ሞታቸውን ያስቸኮሉትን ሳይጨምር ነው። በአንድ መንፈሳዊ በሚመስል ግን ባልሆነ ትምህርት ምክንያት ሰዎች





ንብረታቸውን ከተበዘበዙ፥ አካላቸውን ከተጎዱ፥ በቁጥር የበዙ ብቻ ሳይሆን አንድ ሰውም እንኳን ለሞት ቢዳረግ ያ የአደጋና የማስጠንቀቂያ ጥሪ ሊሆን የተገባ ነው። ዝም መባልም የለበትም።

# አሜሪካዊ ክርስትናና ኢትዮጵያዊ ነጸብራቅ

አንድ ኢራቃዊ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ክርስትና በተለያዩ አገሮች እንዴት እንደሚታይ ባቀረበው የጥናት ጽሑፍ ላይ፥ ክርስትና በተጀመረበት በቅርብ ምሥራቅ ውስጥ ሃይማኖት፤ በግሪክ ፍልስፍና፤ በሮም አውሮጳ ድርጅታዊ ተቋም፥ እንዲሁም በአሜሪካ ደግሞ ማትረፊያ ንግድ ሆኖአል ማለቱን ከአንድ ሰባኪ ሰምቼ ነበር። ይህን በደፈናው እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ባይቻልም በዘመናት ከሆኑት ነገሮች አንፃር ሲታይ አባባሉ መጠነኛ እውነትነት አለው። በዘመናዊው ዓለም ሃይማኖት የሰዎች መሳሪያ፥ ኢየሱስም ማትረፊያ እየሆኑ መጥተዋል።

የሰሜን አሜሪካ አብያተ ክርስቲያናት በወንጌል ስርጭትና ሚስዮናውያንን በመላክ እጅግ ያሸበረቀ ሚና መጫወታቸውን ያለፉት ሁለት መቶ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምስክር ነው። ይህ ሚስዮናዊ ሚና የዚህ ጽሑፍ ዓላማ አይደለምና ብዙ ልልበት አልችልም። ይሁን እንጂ የዘመን አመጣሹ ካሪዝማዊ ስሕተት ሙሉ በሙሉም ባይሆን እንደ ዋና ምንጭ ሊጠየቅ የሚገባው ሰሜን አሜሪካዊ ክርስትና ነው። ለዚህ *በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች* መጽሐፍ 3ኛ ምዕራፍ ላይ ብዙ ተብሎአል። ይህ ዘመን በአጠቃላይ ሲታይ በአውሮጳ ክርስትና በእጅጉ እየተዳከመ ሲሄድ በአሜሪካ ደግሞ እየቀጠነ፥ ዓይነቱም እየበዛና እየተቀየጠ (*syncretism* የሚባለው ይህ ነው) አዳዲስ ትምህርቶችና ልምምዶችም እንደ አሸን እየበዙ የመጡበት ዘመን ነው። ቅይጥነታቸው አንዱ ከሌላው ጋር ለመቻቻል የሚደረገው ሙከራ ሲሆን ይህ ቅይጥነት ዘመናዊ ስምና መልክ እየተሰጣቸው ከመጡት ምሥራቃውያን ሃይማኖቶች ጋርም ጭምር ነው።

የኮሚኒዝም ፍልስፍና በአገራችን ከታወጀ በኋላ ብዙዎች በስደትም ያለ ስደትም ከአገር ወጥተዋል። ፍልሰቱ ክርስቲያኖችንም ይጨምራል። በነዚህ ዓመታት የብዙዎቹ መሸሻና 'የተስፋ ምድር' የሆነው ይህ የሰሜን አሜሪካ አሕጉር ነው። ከነዚያ ዓመታት በኋላ በቀጥታም በተዘዋዋሪም በጽሑፍም፥ በቪዲዮዎችና በድምጽ ካሴቶችም ይወነጨፉ የጀመሩት ትምህርቶች በአገራችን ክርስትና ላይ አሉታዊ ተጋቦት አሳድረዋል። በኋላ ለተፈጠሩት የስሕተት ልምምዶችና ትምህርቶች ቀጥተኛ ምንጭ የሆኑት እነዚህ ናቸው።

ቦታው ብቻ ሳይሆን ጊዜውም በኛ አቆጣጠር 1970ዎቹ መሆኑ የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አለውና ይህም ሊስተዋል ይገባዋል። ከዚያ ጊዜ፥ ማለትም ከ70ዎቹ ቀደም ሲል በአሜሪካ የነበረው ክርስቲያናዊ ባህልና መንፈሳዊ ጥማት እየቀዘቀዘ የመጣበት ጊዜ ነው። ከ1930ዎቹ ትልቁ የምጣኔ ሀብት ቀውስና ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ አሜሪካ ከገባችባቸው የጦርነቶች ቀውስ ውስጥ የወጣችበትና የተደላደለችበት ዘመን ነው። ከ2ኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተወለዱት ያንን ሰቆቃ እንደገና እንዳያዩ ጥረት ተደርጎአል። በጥረቱም ምጣኔ ሀብትና የገንዘብ ኃይል በጣም አደገ። ሳይንስና ቴክኖሎጂም መጠቁ። የዘርና የቀለም መድልዎ ቢኖርም የማኅበራዊ ደኅንነት መርሆዎች እየተሻሻሉ መጡ። ውስጣዊ እርካታና መንፈሳዊ እረፍትን ግን በነዚህ ውጪያዊና ቁሳዊ ነገሮች መተካት አልተቻለም። *የኢየሱስ ትውልድ ወይም የኢየሱስ ንቅናቄ* የተባለው የ60ዎቹ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ለዚህ እርካታ ላጣ የወጣቶች ትውልድ ኢየሱስን በማስተዋወቅ ረገድ በራሱ ስልት አስተዋጽዖ አበርክቶአል። ሆኖም ከነበረበት አሠርት፥ ማለትም ከ1960ዎቹ አልዘለለም።

በነዚህና በቀጠሉት በርካታ ዓመታት ከቢሊ ግሬሃም የጅማ የወንጌል አገልግሎት ሌላ ትልቅ ትኩረት የሳበ አገራዊ የወንጌል እንቅስቃሴ አልነበረም። ይሁን እንጂ በክፍለ ዘመኑ መግቢያና ከዚያም በፊት ተዘርተውና ተጽፈው የነበሩት የካሪዝማዊ ትምህርት ዘሮች በ1950ዎቹ እንደገና ከአዳዲስ ቅርንጫፎች ጋር ማቆጥቆጥ ጀምረዋል። በ1970ዎቹ ደግሞ መበርከትና ሌሎችም ትናንሽ ከቤተ እምነት ነፃ የሆኑ ማኅበሮችና በርካታ አገልግሎቶች እየተመሠረቱ መንቀሳቀስ ጀምረዋል። በተመሳሳይ ጊዜም በኢትዮጵያም ካሪዝማዊ ወይም ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ስር መስደድ ጀምሮአል።

ታዲያ በርካታ ኢትዮጵያውያን በሄዱባቸው በነዚያ ዓመታት ውስጥ ከላይ የተባሉት ውስጣዊ ንቅናቄዎች በጣም ትልቅ ሆነው ጠንካራ ተጽእኖ ባያሳድሩም የታወቁ ግን ነበሩ። በኋለኞቹ የኮሚኒዝም ፍልስፍና አስቸጋሪ ዓመታት ከአገር የወጡ በርካታዎች እንደ ተስፋ ወደሚያዩአት አገር ከመድረሳቸው በፊት በጎረቤት አገሮች የስደት ቦታዎች በቆዩባቸው ጊዜያት ክርስቶስን ማወቃቸው አጋጣሚ ሊባል የማይገባው ነገር ነው። እግዚአብሔር ያንን የመከራና የጭንቀት ከበባ ብዙዎች ወደ እርሱ የሚጠጉበት መጥሪያና መሳቢያ አድርጎት ነበር። ጥቂት ያልሆኑት ወደሚሄዱበት ከደረሱ በኋላ በእምነታቸው የሟሙ ቢኖሩም ብዙዎች በጥንካሬ አሉ።

የነዚያ ዐሠርቶች ስደት ሕዝቦችን ያመሳቀለና ከስፍራ የነቀለ ዓለም አቀፋዊ ክስተት እንጂ እንጂ በአንድ አገር ወይም ወገን ብቻ ላይ ያተኮረ አልነበረም። ኢትዮጵያም ከብዙዎቹ የስደት ሰልፈኞች አንድዋ ናት እንጂ ብቸኛዋም አልነበረችም። ከተሰደዱት ውስጥ በርካታ ክርስቲያኖችም በተለያዩ አቅጣጫዎች ወጥተው





ሄደዋል። ብዙዎቹ እንደ ኢትዮጵያው ክርስትና እንደራሱ በወጣት ዕድሜ የሚገኙ ነበሩ። ይህ ባህላዊውን ሃይማኖት ሳንነካው ነው። ሌላው አጋጣሚ ከአገር ውስጥ የወጡትና በአሜሪካ ኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናትን የመጀመርና የማደራጀት ኃላፊነትን የወሰዱ ወይም የተቀበሉት ሰዎች በአንድ መልክ ወይም በሌላ ከካሪዝማዊ ወይም ጴንጤቆስጣዊ ልምምዶች ጋር የተያያዙ መሆናቸው ነው። ከዚህ ሁኔታ የተነሣ የሰሜን አሜሪካ አብዛኛዎቹ፥ በሙሉ ማለትም ይቻላል፥ አብያተ ክርስቲያናት አንድ መልክ ነው የነበራቸውና አሁንም ያላቸው። ያም በካሪዝማዊ ንቅናቄዎች የቀለመ ጴንጤቆስጣዊ መልክ ነው። አብዛኞቹ በስም ብቻ ነው ወንጌላዊ የሚባሉት እንጂ በአስተምህሮ ረገድ አይደሉም። አንዳንዶቹም ስለመቻቻል ተብሎ ኅብረት እየተባሉ ቢጠሩም ከስም በቀር ቅርጻቸውም ይዘታቸውም ጴንጤቆስጣዊ ቤተ ክርስቲያን ነው። ጴንጤቆስጣዊና ወንጌላዊ የሚሉት አጠራሮች አንድ አለመሆናቸውን አንባቢ ሊያስተውል ይገባል። ይህ ጴንጤቆስጣዊ ቅርጽና ይዘት ጠቅላላውን ባይሆንም አብዛኛውን የአሜሪካ ኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚመለከት እውነት ነው። በእስታቲስቲክስ ረገድ ከበርካታ ትልልቆች የሰሜን አሜሪካ ከተሞች ኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች ቁጥርና አማኙ ሲነጻጸር ከ1.5% እስከ 3.5% ብቻ ነው። ይህ ከአገር ቤቱ አማካይ መቶኛ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር በጣም ያነሰ አኀዝ ነው። የብዙዎቹ አጥቢያዎች ትኩረትም ከወንጌል ስርጭት ይልቅ ከዚያ ለተረፈው ለሌላው ሁሉ ነገር ነው።

ከአብዮቱ ጥቂት ቀደም ሲልና በተለይም በአብዮቱ ዘመናት በአገር ውስጥም ወንጌላዊ ክርስትናና ጴንጤነት ሞክሼ ሆነዋል። ይህ የአጋጣሚ ስያሜ ነው። ቀደም ባሉት ጊዜያት ወንጌላዊ ክርስቲያኖች በየኖሩባቸው ቦታዎች ‘አማኞች’ ወይም ‘የኢየሱስ ሰዎች’ በመባል ነው ይጠሩ የነበረው። ጴንጤ የሚለው ስም ጴንጤቆስጣውያኑ ‘ክርስቲያን’ ከሚለው መጠሪያ ይልቅ የሚጠቀሙበት ቃል ነው። ይህና በተለይም በናዝሬት፥ በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተማዎች በኅብረተ ሰቡ ዘንድ ጥሩነት ከሌላቸው ልምምዶች ጋር በመጣበቅ የተዋሕዶ ተከታይ ያልሆነው ክርስቲያን ሁሉ በጴንጤ ወይም በጅሆቫ ወይም መጤ ስም ታወቀ። ይህንን ስም ከአማኙ ኅብረተሰብ ወይም ወንጌላዊው የክርስቲያን ጎራ ይልቅ አማኝ ያልሆነው ሕዝብ አብዝቶ አወቀው። በእምነትም ሆነ በልምምድ ጴንጤቆስጣዊ ያልሆኑትም ሁሉ ይህን ስም ያለችግር እስኪቀበሉት ድረስ ስያሜው በሁሉ ላይ የተርከፈከፈ ነበር።

በዚያው ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የስደት ገፈት ዘመኗ ነበርና ስም ትልቅ ቁም ነገር ያለው ጉዳይ አልነበረም። ይህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኖች የተዘጉባቸው፥ የወንጌል እንቅስቃሴዎች የተወሰኑባቸው፥ አንዷት አጥቢያ ብዙ ትንንሽ ሆና ያመለከችባቸው

ዓመታት ነበሩ። እነዚህን ብዙ ትንንሽ ቡድኖች ለማገልገል በርካታ አገልጋዮች አስፈለጉ። በብዙ ረገድ ስደቱ ድንገተኛ ይመስላልና በቂ የአገልጋዮች ዝግጅት አልነበረም። እንደ ስደቱ ሁሉ ድንገተኛ አገልጋዮችም በዙ። በአንዳንድ ቦታዎችም ልክ ደርግ በታጠቅ ማሰልጠኛ የ3 ወር ለብ ለብ ስልጠና ሚሊሻዎች አሰልጥኖ ወደ ሱማሌ ግንባር እንዳሰማራው የነበረ በአጫጭር ጊዜ ትምህርቶች የሰለጠኑ የቡድን መሪዎች ተመረቱ። እያንዳንዱን ትንንሽ ቡድን መያዝ ራሱን የቻለ ችግር ነበርና በአንዲት አጥቢያ ብቻ እንኳ መሪዎቹን የመሰሉ ጉራማይሌ ቡድኖች እያደጉ መጡ። ጊዜው ለብዙዎቹ በቂ መንፈሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ ስንቅ ያልነበረበት፥ የትምህርትና የስልጠና መጻሕፍት ጠንቅቀው ያልተዘጋጁበት፥ አዲስ ኪዳን እንኳ እንደልብ ማግኘት ያስቸገረበት ጊዜም ነበር። በችግር ጊዜ የተወለዱ ወይም የሚያድጉ ልጆች ለመኖር በሚያደርጉት ትግል ይጠነክራሉና ስደቱ ራሱ መጠንከሪያ ነው ሊባል ቢቻልም የምዕመናን ቀለብ ግን የዕለት ጉርስ ዓይነት ነበር። አጋጣሚ ሆኖ በነዚሁ ጊዜዎች ውስጥ ነበር እነዚህ የአሜሪካዊ ክርስትና ትምህርቶች በተለይ በቪዲዮ ቴፖች ውቅያኖስ እየተሻገሩ ወደ አገር ውስጥ በብዛት የገቡት። ቀድሞ በነበሩት ላይ እየተጨመሩና እየተባዙ አዳዲስ ትምህርቶችና ልምምዶችም በእጅጉ ተባዙ።

ጠለቅ ብለን ስንመለከተው የ66ቱ ሕዝባዊ አብዮትና ቀጥሎ የተመረጠው ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮት ጎዳና ለቤተ ክርስቲያን ያመጣላት ጥቅምም፥ ያመጣባት ጉዳትም እምብዛም የለም። እርግጥ የማምለኪያ ቦታዎች ተዘግተዋል፤ ንብረት ተወርሶአል፤ ተዘርፎአል፤ ጥቂት ያልሆኑ ታስረው ተጎሳቁለዋል። የቤተ ክርስቲያን ጉዳት ከተቆጠረ ግን ከዚህ ሌላ የለም። ያመጣላት ጥቅምም የለም። እርግጥ መጠነኛ ጥራት የጅምላ ጉዞን የለወጠ መስሎአል፤ እምነትም ዋጋ የሚጠይቅ መሆኑ ታይቶአል። እነዚህ ግን ስደትና አብዮት ቢኖሩም ባይኖሩም በዘመናትና በታሪክ ውስጥ እንደታየው የክርስትና መለዮ መሆን ያለባቸው ነገሮች ናቸው። አብዮቱ የገዛ ራሱን ሥራ ነው የሠራው። የወደቀውም የመውደቂያው ጊዜ ስለደረሰና ከውስጡ ስለበሰበሰ ነው። ደግሞም ዓለም አቀፋዊው የሶሻሊዝም ርዕዮት ሚዛኑ ስላጋደለበት የፍልስፍናውን ማዝመምና ውድቀት ተከትሎ ነው የኢትዮጵያው አብዮትም የወደቀው። ይህ ክስተት አገራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ ይዘት የታየበት ሁኔታም ነበር።

የደርግ መንግሥት በመጀመሪያዎቹ ዘመናቱ ከቻይና ተሞክሮ በመነሣት የባህል አብዮት የተባለውን ዘመቻ በመጠኑ አካሂዶአል። የዘመቻው አንድ ገጽታ ቤተ ክርስቲያንን በስልታዊ መንገድ ጨርሶ ማጥፋት ነበር። ቢሆንለት ያ መንግሥት ተቃዋሚዎቹን የፖለቲካ ቡድኖች ምሳና እራት እንዳደረገው ቤተ ክርስቲያንንም ሊውጥ ሞክሮ ነበር። ቤተ ክርስቲያን በምድር ብትኖርም ምድራዊት አይደለችምና ይህን ማድረግ አልቻለም። ይህ ከቶም





የማይቻል ነው። ቤተ ክርስቲያን በምድራዊ መንግሥት ቸርነት የምትኖር ወይም በዚያ መንግሥት ስደት የምትጠፋ አካል አይደለችም። ከጌታ ዕርገት በኋላ የነበሩት ሦስት መቶ ዓመታት የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የዚህ ዐቢይ ምስክር ነው።

በአንጻሩ 1980ዎቹ የነጻነቱ ዓመታት ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ ለስደት ሳትሰናዳ እንደመሸባት አሁንም ለነፃነትና ለሰፋ ዕድል ሳትሰናዳ የነጋባት ይመስላል። ወዲያው መንደፋደፍ ተጀመረ። ጊዜውንና ሁኔታውን የተመለከቱ ጠሊቅ ቀርቶ ጠቅላላ የግምገማና የስልት ጥናት ምክክሮችና ጸሎቶች እንኳ በወጉ አልተደረጉም። በወንጌል ስርጭት ላይ ብቻ ሰፊ ሩጫ ተደረገ። ስለዚህ የኮሚኒዝም ካድሬዎችንና የተፈናቀሉ የጦሩንና የምሑራኑን ክፍል ጨምሮ ብዙዎች ወደ ወንጌል እውነት መጡ፤ ወደ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ተደባለቁ። ይህ ትልቅ ዕድል ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከደርግ ዘመን ቀጥሎ በቁጥር ያደገችበት ዘመን እንደኛ አቆጣጠር 1984-85 ነው። የ1987 የእስታቲስቲክስ ቢሮ ዘገባ በግርድፉ እንደሚያመለክተው ጠቅላላው የክርስቲያን አኀዝ 48.65% ሲሆን ሙስሊሙ 44.95% ነው። የቀረው 6.4% ሌሎችን በሙሉ ይይዛል። ከክርስቲያኑ ኀራም ተዋሕዶ 38.15%፤ ካቶሊክ 0.89%፤ ወንጌላዊው ክርስትና 9.61% አስመዝግቦአል። ዓለም አቀፍ እስታቲስቲክስ ደግሞ የወንጌላዊውን እምነት አኀዝ ከ12 እስከ 14% ከፍ ያደርገዋል። ይህ እሰይ የሚሰኝ መልካም ዜና ነው። ይሁን እንጂ፥ ዕድገቱ ጥሩ ሆኖ ሳለ 'ከወንጌል በኋላስ?' የተባለ አይመስልም። መጠነ-ሰፊ ዘመቻ ላይ እንጂ ስረ-ጥልቅ ክርስትና ላይ አልተተኮረም። ስለዚህ በአንድ በኩል ጥቂት ያልሆኑ ወደኋላ ተመልሰዋል። በሌላ በኩልም ከዚያ ካልበለጡ ያላነሱ ለተሳሳቱ ትምህርቶችና ልምምዶችም ተዳርገዋል።

በክፉው ቀን የነጎዱትም እንደድል ማግስት አርበኞች ከነአሜሪካዊ ልምምዳቸው መጡና በቀደሙት ዘመናት የቃረሙትን የተደበላለቀ ትምህርት ሳይመርጡ ለአገር ቤቱ ምዕመናን አጋቡት። ቤተ ክርስቲያንም ዘመኗን መምሰል ጀመረች። የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ዘመን አይደል የውድድር? ቤተ ክርስቲያንም ውድድር ውስጥ ገባች። የዲሞክራሲ ዘመን አይደል? ማን ማንን ይነካል? ማንስ ማንን ይናገራል? ሕገ መንግሥታዊ ድጋፉም ሌላ ጉልበት ማበርከቱ አይረሳም። ስለዚህ ተንሳፋፊና ተለጣፊ አብያተ ክርስቲያናት በዙ። አንዳንዶቹም የአኩራፊዎች መሰብሰቢያ እየሆኑ ገና በሚከፈቱበት ዕለት ሺህ ሲደመር እየሆኑ መሰብሰብ ጀመሩ። በዚህ ሁሉ ወንጌል ተሰራጭቶ ነፍሳት መዳናቸው ተአምር ሆኖ ሳለ የስሕተት አሠራሮችም መብዛታቸው አሌ የማይሉት እውነት ነው። የጠፉትን በማጥመድ ፈንታ የዳኑቱን ከቤተ ክርስቲያን ቤተ

ክርስቲያን የሚያንገዋልሉት አማኞችና አገልጋዮችም ሌላ በአጥቢያዎች መካከል የሚፈጠሩ የችግር አጀንዳ ናቸው።

ከላይ በተጠቀሱት ጊዜያትና ከኢትዮጵያውያኑ አሜሪካዊ ክርስትና ጋር የተያያዘው ሁኔታ ከምርቱ ይልቅ ግርዱ የበዛበት ነው። በሰሜን አሜሪካ የሚገኙት የብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ክርስትና ከመጽሐፍ ቅዱሳዊነት ይልቅ አሜሪካዊውን ካሪዝማዊነት ሙጥኝ ብሎ ከረመ። ይህም፥ ጤንነትን፥ ብልጽግናን፥ ድሎትንና ምቾትን፥ ልምምዳዊነትን፥ ስሜታዊነትን፥ ከሞት መሸሽን፥ ከመስቀል ዋጋ የተለየ ክርስትናን ማስተዋወቅ መለያው ሆነ። ከላይ የተጠቀሰው ሰው ክርስትና በአሜሪካ ማትረፊያ ሆነ እንዳለው በኢየሱስ ስምም እየተነገደ መጣ። አንዳንዶች አገልጋዮች ደግሞ በቪዲዮ የሚያዩአቸውን ሰዎች ቃል በቃልና እርምጃ በእርምጃ እየኮረጁ እንደ በቀቀን መድገምን ሥራዬ ብለው ያዙት። ክርስትና የሚጠይቀውን ዋጋ መክፈል የማይወድ ሁሉ ደግሞ ተሻምቶ ተቀበላቸው። አንዳንዶች በየዋህነት አንድ ሰው ከዚያኛው የዓለም ክፍል ስለመጣ ብቻ የተማረና ለአገልግሎትም የበቃ አድርገው ይቀበሉታል። ይህ አደገኛ የዋህነት ነው።

አንድ ሰባኪ ከአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን አምልኮ ጋር በማነጻጸር የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና አምልኮ አለማወቁን፥ አለመጀመሩን ተና ግሮ ነበር። በነጻነት ስም አምልኮን በሚመስልና ነገር ግን ሥርዓት በለቀቀ ሁኔታ የፈለጉትን መሆን ለግንፍል ስሜታዊነት በር መክፈት ነው። መፈክራምነትና 'ትቅደምና ይውደም' ሲል የኖረ ኅብረተሰብ በበዛበት በዚህ ዘመን አምልኮ ያለመፈክርና ያለጩኸት የሚደምቅ የማይመስላቸው ብዙዎች ተነሡ። በእውነቱ፥ አምልኮ በቅርጹ አንድ ዓይነት መሆን የግድ የለበትም። የአምልኮ ዓላማና ግብ የአምላኪ ከተመላኪው ጌታ ጋር መሆንና በዚያ መቆየት ነው። ሚዛኑም የተጠበቀ ሊሆን ይገባዋል። የማኅበር አምልኮም የጉባዔተኛው በጸሎትም በዝማሬም፥ ቃሉን በመማርም፥ ወይም የመሳሰሉትን ነገሮች በማድረግ አብሮ መቆየት ነው። ከጩኸታም አምልኮ ልምምድ ወደ ጸጥተኛ ጉባዔ የሄደ ሰው የእንቅልፋሞችና የሙታን ጉባዔ እንደገባ ሊመስለው ወይም ከጸጥተኛ አምልኮ ጉባዔ ወደ ጩኸታሙ የገባው የቀውሶችና የዕብዶች አደባባይ የገባ ሊመስለው ይችላል። የጸጥታና የጩኸቱ ልዩነቱ አንጻራዊ ነው። የሁለቱም ይዘት ተመሳሳይ ከሆነ ቅርጻቸው ብቻ ነው ልዩነቱ። ይህ እንግዲህ ለአምላኪው ምዕመን ነው። አዲስ ለሚመጣውና ላላመነውስ? ይህም መታለፍ የለበትም። በቃሉ ውስጥ የተጻፈውን ንድፍ ተከትሎ ሚዛናዊነትን ማስፈን የጉባዔ አምልኮ ጤናማ ግብ ነው። ክርስትናውና ትምህርቱ ጤናማ እስከሆነ ድረስ የአምልኮ ቅርጽ የጉባኤውን ሚዛንና ጣዕም እየተከተለ የሚቀረጽ ወይም የሚመቻች ነገር ነው። የሚቀረጽና የሚመቻችም ብቻ ሳይሆን የጉባኤው ዕድገትና ብስለት በራሱ የሚለውጠው ወይም





የሚያመጣውም ሊሆን ይችላል። አንድ የአምልኮ ሥርዓት በሌላው ላይ ሊያይልና ሊልቅ የሚችልበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም፤ ወይም አምልኮ በአዝጋሚ ለውጥ እያደገ የሚሄድ ነገር አይደለም። በዚህ ዘመን ያለን እኛ የዛሬ 20 ወይም 200 ዓመት በፊት ከነበሩት የተሻለ ልናመልክ አንችልም። ወይም እዚህ ያለን እኛ ቻይና ወይም ቻድ ካሉት ክርስቲያኖች የተሻለ ልናመልክ አንችልም። አምልኮ በጊዜና በቦታ ልቀቱ ሊበላለጥ አይችልምና።

ሌላው የዘመናዊው መነቃቃትና ተሐድሶ ንቅናቄዎች፥ በተለይም የአሜሪካዊው ክርስትና ገጽታ ንዋይና ብልጽግና ነው። ይህ ለሁሉም ዓለማዊ አእምሮና ለምዕራቡ አመለካከት፥ እንዲሁም ለሥጋዊ ክርስቲያን የሚመች ትምህርት ነው። የምዕራቡ ዓለም ሥርዓተ ማኅበር የሆነው ካፒታሊዝም በተፈጥሮው ሰዎችን መፍቀሬ ንዋይ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ክርስቲያኖችም ከዚህ ነጻ አይሆኑም። በምዕራቡ ካፒታላዊ ዓለም ለገንዘብ ፍቅር ብቻ ሳይሆን ለገንዘብ ማካበትም ጣሪያው ሰማይ ነው። ግን ልፋቱም የዚያን ያህል ነው። ስለዚህ ያለልፋት የሚገኝ ከሆነ፥ አቋራጭ መንገድ ከተገኘ ማለፊያ ነውና ለምን ይህ መንፈሳዊነትን የተቀባ ትምህርት ሰዎችን አይስብም? የብልጽግና ወንጌል ስለሚባለው የስህተት ትምህርት በመጀመሪያው መጽሐፍ በቂ ተብሎአል። ከዚህኛው ርዕስ ጋር በተያያዘ ጥቂት መጨመር ያስፈልግ ይሆናል።

የሰዎችን የገንዘብ ምንጭ የሚመጥጡ ስግብግብ አስተማሪዎች የሚያስተምሩአቸው ጥራዝ ነጠቅ ጥቅሶች አሉ። እርግጥ ጌታ ስጡ ይሰጣችኋል ብሎአል። ጳውሎስም በጥቂት የሚዘራ በጥቂት እንደሚያጭድ ከሚቀበልም የሚሰጥ የተባረከ እንደሆነ ጽፎአል። ግን ይህ ብቻ አይደለም። እነዚህ የማትረፊያው ኢየሱስ አስተማሪዎች የሆኑ የወንጌል ነጋዴዎች 2ቆሮ. 8 እና 9ን ቢያጠኑት በቂ ትምህርት ያገኙ ነበር። የቆሮንቶስ ሰዎች ከድኅነታቸው ሳይቀር ይለግሱና ይሰጡ የነበረው ለፈዋሹ፥ ለቀዳሹ፥ ለሰባኪው፥ ለአስተማሪው ጳውሎስ ሳይሆን ለተቸገሩት የኢየሩሳሌም ምዕመናን ነበረ። የሰጡትም ቤተ ክርስቲያን መርጣ በሾመቻቸው ሰዎች እጅ ነበር፤ 1ቆሮ. 16፥1-4።

አሟጥጠው ሰጥተው ኋላ ጎድሎባቸው ራሳቸው የሚበሉትን አጥተው እንዳያማርሩ በደስታና በፈቃድ ካላቸው እንዲሰጡ ነው የተባሉት እንጂ የውሸት ተስፋም ማስፈራሪያም አልተነገራቸውም። አንድ የብልጽግና ትምህርት ሰባኪ ያላቸውን አሟጥጠው መስጠት እንዳለባቸው ሲያስተምር እንደ ምሳሌ የጠቀሳት የሰራፕታዋን ሴት ነበር። 'ይህች ሴት ያላትን አሟጥጣ መጋገርዋ ምን አሳጣት?' አለ። አንደኛ ይህች ሴት ያላትን አሟጥጣ አልጋገረችም፤ ከቀራት ትንሽ ቀንሳ ጋገረች እንጂ። ሁለተኛም እንደ ኤልያስ ቃል ሴቲቱና ልጅዋ በረሃቡ ዘመን ሁሉ አልተራቡም። እነዚህ የዘመና ችን አትራፊዎች ግን የባንክ ገንዘብ አሟጥጠው ወስደው ቤትና

ንብረት ሲያስሸጡ፥ የታክሲ ሳንቲም ወስደው በእግር ሲያስኬዱ፥ ሌላው ቀርቶ ሰዎችን ሲያስርቡ ታይተዋል።

እርግጥ ለእግዚአብሔር ከሰጠን እርሱም እንዲባርከን ብንመኝ ወይም ብንጠብቅ ክፋት የለበትም። ግን እንዲህ ወይም እንዲያ ስላደረግን እግዚአብሔር እንዲህ ወይም እንዲያ እንዲያደርግልን ግዴታ አለበት ወይ? ወይስ እኛን እነርሱ እንደሚሉት ሊያበለጽገን ተስፋ ሰጥቶአል ወይ? የማትረፊያው ኢየሱስ አስተማሪዎች፥ 'አዎን ተስፋ ሰጥቶአል' ነው የሚሉት። መስጠትን በመዝራትና ማጨድ ሕግ አስደግፈው ብር ሰጥቶ ብሮች መቀበል እንደሆነ ያስተምራሉ። ክርስትና እንደምን ፈጥኖ ተለወጠ? ከዓመታት በፊት ብቻ እንኳ ይሰበክ የነበረው ስብከት ክርስትና ዋጋ ማስከፈሉ፥ የኛ የሆነው ሁሉ የክርስቶስ መሆኑ፥ ደቀ መዝሙርነት መስዋዕትነትን መጠየቁ ወዘተ ነበር። ዛሬስ? ዛሬ የሚሰበከው ክርስትና ዋጋ እንደሚያስገኝ፥ የክርስቶስ የሆነው ሁሉ የኛ መሆኑ፥ ምንም መስዋዕትነት ከቶ እንደሌለ ነው ለጆሮ ተጣፍጦ ተቀምሞ የሚነገረን። ወንጌሉ ነው የተለወጠው ወይስ ሰዎቹና ትምህርቱ?

ጌታ ሲጠራን ለክርስቲያኖች ሁሉ የብልጽግናን ተስፋ ሰጠ? አዎን፥ ሰማያዊና ዘላለማዊ ተስፋን ሰጥቶአል። ጊዜያዊና ምድራዊ ብልጽግናስ? የተስፋ ሻሞ የሚበትኑልን ብዙ ቢሉም የለም፥ አልሰጠም። ለምድሩማ ራሱም ራሱን የሚያስጠጋበት እንዳልነበረው ነው የተናገረው። ደቀ መዛሙርቱስ? ጴጥሮስና እንድርያስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ ዓሳቸውን መረባቸውንና ታንኳቸውን ትተው ሲከተሉት የትልልቅ መርከቦችና የሰርዲን ፋብሪካዎች ባለቤቶች መሆን ነበረባቸው። ግን በሐዋ. 3፥6 ላይ ጴጥሮስ ብርና ወርቅ እንደሌለው ነበር የተናገረው። ዮሐንስም የብር ከረጢቱን አልከፈተም፤ የለውማ። ጳውሎስ እስኪዚያች ሰዓት ድረስ እንደሚራብ እንደሚጎሳቆል መከራውን ዘርዝሮ 'እኔን የምትመስሉ ሁኑ' ይላቸዋል፤ 1ቆሮ. 4፥11-16። ይህ ማለት ሁሉ ክርስቲያን ጎስቋላ ይሆናል ማለት አይደለም። የዚያኑ ያህልም ሁሉም ክርስቲያን ስለሆነ ብቻ የተንደላቀቀ ባለጸጋ ይሆናል ማለትም አይደለም። በመጀመሪያ ከደኅንነትና የዘላለምን ሕይወት ከማግኘት የበለጠ ምንም ብልጽግና የለም። ቀጥሎም ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ባለአደራ በተሰጠው ምድራዊ ጸጋ ታማኝና ትጉህ ከሆነ፥ ከአምላኩ በተቀበለው ጉልበት፥ አእምሮና ጥበብ በተግባሩ ከተሰማራ ፍሬያማ የማይሆንበት ምክንያት የለም። ብር ግን እንደቅጠል ከዛፍ ላይ አይቀነጠስም።

የብልጽግና ትምህርት ለስግብግብ አእምሮና ለሥጋዊ ክርስቲያን በጣም የሚጥም ትምህርት ነው። ከሁሉም የሚያሳፍረው ደግሞ





ይህ ትምህርት በአንዳንዶች ዘንድ ከደኅንነት ጋር መቆራኘቱ ነው። የዳነ ሁሉ መበልጸግ አለበት፤ ይህ ካልሆነ ደኅንነቱ አጠያያቂ ነው እስከማለት ይደርሳሉ። ለቤተ ክርስቲያንና ለጤናማ አገልግሎቶች መስጠት ተገቢ ቢሆንም መስጠትን የብልጽግና መክፈቻ ያደርጉታል። በመስጠት ብቻ መበልጸግ ቢኖርማ ኖሮ ጳውሎስ ለኢየሩሳሌም ችግረኞች እርዳታን ከገላትያና ከመቄዶንያ ከቆሮንቶስም አብያተ ክርስቲያናት ከመሰብሰብ ይልቅ ለራሳቸው ለኢየሩሳሌም ሰዎች ይህን አቋራጭ መበልጸጊያ ለምን አላስተማራቸውም ነበር? ሰጥተው ራሳቸውን እንዲያበለጽጉ ማስተማር ሲችል ለምን ዙሪያ ጥምጥም መሄድ አስፈለገው? የብልጽግና አራማጆች ትምህርትና ባህርይ የሚጋጭበት ትልቅ ነጥብ እነዚህ ሰዎች በአብዛኛው መቀበል እንጂ መስጠትን የማያውቁ ሰዎች መሆናቸው ነው። አድማጮቻቸው እንዲሰጡ ያስተምራሉ እነርሱ ግን አይሰጡም። በዚህ ነገር ከልብ የሚያምኑ ቢሆኑ ኖሮ ለችግረኛ ፈጥኖ ደራሽ እነርሱ በሆኑ ነበር። ግን በዚህ ምግባረ ሠናይ የሚታወቁ አይደሉም። ይህ የሚያሳየው ትምህርቱን ራሳቸውም እንደማያምኑበትና ለማትረፊያነት ግን እንደሚገለገሉበት ነው።

ሌላው አሳሳቢ ነጥብ ደግሞ ይህን የሚሰብኩላቸው ወይም አድማጮቻቸው አድርገው የሚመርጡአቸው ሰዎች በመጠኑም ቢሆን ያላቸውና ሊሰጡ የሚችሉ መሆናቸው ነው። እንዲህ ያለ ትምህርት የሚሰብኩ ሰዎች ወደ ድሆች ወይም ወደ ችግረኛ ቤተ ክርስቲያን ወይም ችግረኞች አማኞች ዘንድ ሲሄዱና ይህን ሲናገሩ አይታዩም። ቢሆንማ ለማበልጸግና ድኅነትም ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ወደ ድሆቹ መሄድ ነበረባቸው፤ ግን የሚተላለፍባቸው ይመስል ድህነትን ይፈሩታል፤ እንደማይሰምርላቸውም ጠንቅቀው ያውቁታል። መቀማጠል የእግዚአብሔር ልጅነት ምልክትና መታወቂያ ቢሆንማ ኖሮ በርካታ አማኞች የጌታ ልጆች ሆነው ሳሉ ከእምነታቸው ብቻ የተነሣ በመከራና በስደት ስለምን ይኖራሉ? የለም፥ የብልጽግና ወንጌል ልዩ ወንጌል ነው። የብልጽግና ትምህርት ነዢዎችና በአጠቃላይ የካሪዝማውያን ሌላ ጉልህ ችግር ለእግዚአብሔር ያላቸው ግምት ትንሽ ነው። እግዚአብሔርን የተጠየቀውን ሁሉ የሚያቀርብ ፈቃድ የሌለው የፍጡራኑ አገልጋይ አስመሰሉት። እኛ የእርሱ አገልጋዮች ልንሆን ሲገባ እርሱን የኛ አገልጋይ አድርገው ሳሉት።

እግዚአብሔርን አገልጋይ የሚያስመስለው ሌላ ትምህርት የጸሎት አመላለሱ ነው። እግዚአብሔር ጸሎትን ይመልሳል? አዎን፥ በእርግጥ ይመልሳል። ግን እኛ እንደፈለግን ይመልሳል? አይደለም። በኛ ምኞትና በእግዚአብሔር ፈቃድ፥ ወይም በምንፈልገውና በሚያስፈልገን ነገር መካከል ያለውን ልዩነት እንዲህ በቀላል መመልከት የለብንም። ከእነዚህ አንዳንዶች

እግዚአብሔር የልባችንን መሻት እንደሚሰጠን በመናገር መዝ. 37፥4ን ጎምደው ይጠቅሱታል። ከጥቅሱ ብቻ እንኳ ስንመለከተው እግዚአብሔር የልባችንን መሻት የሚሰጠን ልባችን ስለተመኘው ብቻ አይደለም። በእርሱ ደስ መሰኘት አብሮ ተጠቅሶአል። በእርሱ ደስ መሰኘት ለፈቃዱ መገዛትን የያዘ እውነትን ነው። እንዲያም ሆኖ በእርሱ ደስ የተሰኙትም እንኳ ለምነው የልባቸውን መሻት ያጡባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው።

ከላይ በትንሹ እንደተጠቀሰው እዚህ ላይ እንደገና ሊጤን የሚገባው የሰሜን አሜሪካ ክርስትና ወይም አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ እንዲህ ናቸው ማለት ያለመሆኑ ነው። የጅምላ አባባል ሁልጊዜም ስሕተት አይጠፋውም። ተፈትኖ ያለፈ ፍሬያማ ክርስትና እና አገልግሎት ያለባት አገርም ናት አሜሪካ። በሀብትና በምቾት ተከብበው ያንን የመንደላቀቅ ፈተና ገፍተውና ወደጎን ብለው የሚኖሩ ምዕመናንና የሚያገለግሉ ታማኝ አገልጋዮች አገርም ናት አሜሪካ። በድኅነት ጌታን ከማመንና ከማገልገል ይልቅ ምናልባት በድሎት ታማኝ መሆን ይበልጥ ፈታኝ ሳይሆን አይቀርም። አሜሪካ ጠንካራ ወንጌላዊ እንቅስቃሴና ወንጌል ወዳልደረሰባቸው የሕዝብ ክፍሎች ወንጌልን ለማድረስ ዋጋ እየተከፈለ የሚደረግ ብርቱ ትግል የሚታይባት አገርም ናት። ኢትዮጵያም የዚህ የወንጌል ገድል በረከት ተካፋይ ናት። በኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ታሪክ ውስጥ እንደሚታወቀውም እንኳ ከ1910ራዎቹና 20ዎቹ ጀምሮ ብዙ የወንጌል መልእክተኞች ከዚህ ክልል መጥተዋል። አሜሪካዊ ዜግነታቸውን ለአገልግሎት አመቺነት ሲሉ በኢትዮጵያዊ ዜግነት የለወጡ እንደ ዶክተር ቶማስ ላምቢን የመሰሉ ዋጋ ከፋይ ሚስዮናውያን ወደ አገራችን መጥተው አገልግለዋል። ምቾትና አካላቸውን ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውንም መስዋዕት ያደረጉ ጥቂት አይደሉም። አሁንም ቢሆን በዚህ ረገድ ብዙ ነገሮች እየተደረጉ ናቸው። ለቃሉና ለአባቶች እምነት የሚጠየቀውን ሁሉ ዋጋ ከፍለው ጤናማ የክርስትና ትምህርት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የጣሩና የሚጥሩ ውብ አገልጋዮች ያሉባት አገር ናት አሜሪካ፥ በሌላ ገጽታዋ።

እንግዲህ ክርስትና ዓመታትና ዘመናት ሲያልፉና ሲለወጡ እንደየዘመኑ ፋሽን የሚለዋወጥ ከሆነ፥ ከየዘመናቱ ብቻ ሳይሆን ከየአህጉራቱ የሚመጡ ነገሮች ቅይጥም ከሆነ በአዲስ ኪዳን የሚታየው ትክክለኛ መልኩ መልክ ብቻ ሆኖ ሊቀር ነውና መጠንቀቅ ያሻል። የአዲስ ኪዳንን መሠረት የለቀቀና የሚያስለቅቅ ወንጌልን ከአሜሪካ ብቻ ሳይሆን ከሰማይ መላእክትም መጥተው ቢሰብኩልን የጳውሎስን ማስጠንቀቂያ ደግመን ልናጤን ይገባናል፤ ገላ. 1፥8-9፤ 2ቆሮ. 11፥4።





# የአኩራፊዎች ጉባኤ

ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ከላይ ጎልቶ የሚታይ አንድ ዓይነት መልክ ያለው ቢሆንም በማይታይ ሁኔታ ደግሞ ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን አቋርጦ የሚያልፍ ንቅናቄ ነው። ስለዚህ ካሪዝማዊ ባልሆኑ አብያተ ክርስቲያናትም ይህን ትምህርት የሚቀበሉ ሰዎች ሊገኙ ይችላሉ። እነዚህ በካሪዝማዊ እንቅስቃሴ የተወሰዱ ሰዎች በአጥቢያቸው፥ በአገልግሎቶች፥ በአገልጋዮች፥ በመሪዎች ያለመርካት ይጀምራሉ። ማጉረምረምና ውጥረትም ይከተላል። አንዳንዶም ከሥርዓት የወጡ ነገሮችን ማድረግና መለማመድ ይጀምራሉ። ተግሳጽና እርምት ሲሰነዘር ማኩረፍ፥ ብሎም ከዳር መሆንና እንዲያውም ከአጥቢያቸው መውጣት ይመጣል። እንዲህ ያሉቱም በእንቅስቃሴው ዙሪያ መሰባሰብ ይጀምራሉ ወይም ቀደም ብለው የተጀመሩ ከኖሩ ከነዚያ ጋር ለመወገን ይደባለቃሉ።

ከእነዚህ መካከል ከአንድ ቦታ ወጥተው ድንበር ዘልለው እሌላ ቦታ መግባታቸው የማይታወቃቸውም አሉ፥ ልክ እንደ ዘላኖች። እዳር አገር ያሉ የሶማል ዘላኖች ሳርና ጨው የሌለው ውኃ እየፈለጉ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሄዱ ከብት አርቢዎች ናቸው። የከብት መኖ እስከተገኘ ድረስ መሄድና መቆየት ነው። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው በመሄድ ጉዞአቸው ውስጥ ከሶማሊያ ወጥተው ኬንያ ወይም ኢትዮጵያ ወይም ከኢትዮጵያ ወጥተው ሶማሊያ ወይም ጂቡቲ ሲገቡ ኬላና ወታደሮች ባሉበት በኩል ካላለፉ በቀር ብሔራዊ ድንበር መኖሩ ከልብ አይስተዋላቸውም። ግን አልፈዋል። ከአንድ የሥርዓት ክልል ወደ ሌላ የአስተዳደር ክልል አልፈዋል፥ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ገብተዋል። መንፈሳዊ በሚመስሉ እንቅስቃሴዎች መረብ ውስጥ የገቡ አንዳንድ ክርስቲያኖችም ልክ እንዲህ ናቸው። የሚጥማቸውን ብቻ እየፈለጉ ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን እየባዘኑ ሳይተከሉና ስር ሳይኖራቸው በቀላሉ ለመነቀልና ለመወሰድ የተዳረጉ ሆነው ይኖራሉ።

አንዳንድ ጊዜ ትላልቅ መሪ አገልጋዮች በአንድ ወይም በሌላ አሳብ ካልተስማሙ አኩርፈው ወጥተው ማሰባሰብ ይጀምራሉ። አንዳንዴም ከሌላ ስፍራ ወይም አገር የሚመጡት ከነባሮች ወይም ከቀድሞ ቤተ ክርስቲያናቸው ጥላ ስር ወይም ጋር ላለመሆን እንዲሁ ራሳቸውን የሚመስል አገልግሎት በፊናቸው ይከፍታሉ። ውጤቱ ሲታይ ግን ከምንም የተነሣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ ሳይሆን አንዱ ቀድሞ የተሠራበትን እያፈረሱ በፍርስራሹ ሌላ አዲስ መሥራት ነው። ይህ ጤናማ አይደለም።

ታሪካቸውን ቀረብ ብለን ስናጤን የካሪዝማውያን ማኅበራት ዋና የዕድገት ስልት ወንጌልን ወዳልዳኑት በማሰራጨት ሳይሆን

በሌላው ቤተ ክርስቲያን የተጠለሉትን በመጥለፍ ነው። ዓሳን ከባህሩ ሳይሆን ከመረቡ የሚያጠምዱ ናቸው። የጠፉትን ከዓለም ሳይሆን ያመኑትን ከሚያመልኩባቸው አብያተ ክርስቲያናት መጥለፍና ማስኮብለል ደማቅ መታወቂያቸው ነው። አንዳንዶቹ ማኅበራት ገና ከጅምራቸው ማደጉ ከውጭ ሲታይ የጤና ሊመስል ይችላል፤ በቀረቤታ ሲታይ ግን ብዙውን ጊዜ ቀደም ሲል ውስጥ ለውስጥ የተደረጉ ጤናማ ያልሆኑ ውስብስብ ነገሮች ይገኛሉ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተጀመሩ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን አጀማመር ታሪክ ቢያጤኑ ይህን እውነት በቀላሉ መረዳት ይቻላል። በ1980ዎቹ አጋማሽ በአዲስ አበባ አንድ ቤተ ክርስቲያን ገና በተጀመረችበት ዕለት ወደ ሁለት ሺህ ሰዎች ያህል ተገኝተው ነበር። ብዙዎቹ በዚያው ቀርተዋል። ይህ እንዴት ይሆናል ሲባል አንድ ሰው፥ 'ይህ ምን ያስገርማል፥ በበዓለ ኀምሳ ቀን በአንድ ጊዜ 3 ሺህ አልተጨመሩም እንዴ?' አለ። በእርግጥ ተጨምረዋል። ያ ታዲያ እውነተኛ መጨመር ነው እንጂ ከበረት ወደ በረት መነዳት አልነበረማ! እነዚያ ሦስት ሺህ በዚያው ቀን የወንጌል ስብከት ሰምተው ልባቸው ተነክቶ አምነው የዳኑና የተጠመቁ ሰዎች ነበሩ እንጂ ከአንድ ኪስ ወደሌላ ኪስ የተዛወሩ ገንዘብ አልነበሩም።

እርግጥ ነው፥ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በሁሉ ረገድ ፍጹማን አይደሉምና እንከን አያጣቸውም። ቤተ ክርስቲያን ፍጹም ለመሆን እየተሠራች ያለች አካል ናት እንጂ ክርስቶስ መጥቶ እስኪነጥቃት ድረስ ፍጹም አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን በሰዎች የተሠራች አካል ናት፤ ሰዎች ደግሞ ፍጹማን አይደሉም። በእንከኖችዋ አዝኖ ወይም አኩርፎ ከዳር መሆን መፍትሄው አይደለም። አንዳንዶች ቢሻል ለመመለስ ካልሆነም በዚያው ለመውጣት ከዳርና እበር ላይ ሆኖ መቆየትን ይመርጣሉ። ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉቱ በቋፍ የሚገኙ አማኞች ከላይ ላየነው አጉል እንቅስቃሴ ምግብ ለመሆን የተዘጋጁ ናቸው።

## ሒያሲያንን መጥላት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልጋዮች አይሳሳቱም ማለት የዋኅነት ነው። እነ ሙሴን፥ እነ አሮንን፥ እነ ዳዊትን፥ እነ ጴጥሮስን የመሰሉ ብርቱ መሪ አገልጋዮች ተሳስተዋል። ስሕተቱን የሚያኀላው ሌላ ስሕተት የሳቱትን ዝም ማለት ነው። አንዳንድ አገልጋዮች ሲወቅሱአቸው አይወዱም። ያደረጉትን፥ ያስተማሩትን፥ የጻፉትን፥ የሰበኩትን አንስተው አስተያየት ሲሰነዝሩባቸው አይወዱም። ሒስ የስነ ጽሑፍ ቋንቋ ብቻ ወይም ኮሚኒዝም





የቸረን ቃል አይደለም፤ ነባር የሆነ ቃል ነው። አሳቡም ለማፍረስ መተቸት ወይም መተረብ ሳይሆን ገንቢ ለሆነ እርምትና ለማስተካከል መውቀስ፥ መንቀፍ፥ ጥፋትን ማሳየት የማረሚያ ነጥቦችንም ማቅረብ ማለት ነው።

በአማርኛ መዝገበ ቃላት ትርጉም የሄድን እንደሆነ በጥሬ ትርጉሙ ሒስ በደል፥ ገመና፥ የሚያስነቅፍ ነገር፥ ነቀፋ ማለት ነው። ሐያሲም ነቃፊ ከሳሽ ወቃሽ ማለት ነው። ሌላው ትርጉሙ ማሸት፥ ማፍተልተል፥ ማበራየት፥ መርገጥ፥ ማልፋት፥ ማፍረጥረጥ ማለት ነው። ደግሞም የአሉታ አንቀጽ ሆኖ አንድ ነገር ትክክል አለመሆኑን መናገር፥ ማረጋገጥ ነው።[10] ሒስ በዘመናዊና ሰፊ ትርጉሙ ስህተትን ማሳየትን፥ ማስረዳትን የያዘ ነው። በዘመናዊ የትምህርት መስኮች ከአፍራሽነት ይልቅ ገንቢ በሆነ ሁኔታ በማና ቸውም ሁኔታዎች የሚገለገሉበት የግምገማና የእርማት ሂደት ነው። ማሔስ፥ መውቀስ፥ ጥፋትን ማሳየት በየትኛውም ባህል ጤናማ ነገር ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎችና በተለይም በኢትዮጵያውያን ልማድና ባህል እንደ አፍራሽ ተደርጎ ይቆጠራልና ገንቢው ገጽታ ብዙም አድናቆት አያገኝም። ይህ ጥሩ ልማድ ካለመሆኑም ሌላ አንባቢን ወይም አድማጭን በግብዝነት የበለጠ አስተያየት እንዲያቀርብ የሚገፋፋ ነው። በተለይም አወቁ በሰሉ በተባሉት ዘንድ ይህ ነገር ተቀባይነቱ የመነመነ መሆኑ ደግሞ የሚያስገርም ነው። አንዳንዶች ስህተታቸውን ሲጠቆሙ፥ ሲወቀሱ ወቃሾቹን ይጣሉአቸዋል፥ ይጠሉአቸዋልም። በድርጊት ተርጉመን አልተጠቀምንበትም እንጂ 'ወቃሽ መካሪ አያሳጣህ' የሚለው የባህላችን ብሂል የዚህን ነገር ጤናማውን ገጽታ የሚያሳይ ነው። ብዙዎች ማፈሪያ ስለሚመስላቸው ይሸፍኑታል። በሕይወት ውስብስብ ጕዞ ውስጥ መሳሳታቸው ተነግሮአቸው ወይም ራሳቸው ተረድተውት 'ተሳስቼ ነበር' የሚሉና የሚናዘዙ ጥቂቶች ናቸው። አንዱን እውነተኛ ተናዛዥ በሚቀጥለው ርዕስ እናየዋለን።

ስሕተትን መጠቆም የግድ ከዚያ ከተሳሳተው ሰው የተሻሉ ሆኖ የመገኘት ምልክት አይደለም። እርሱ ካላየው አቅጣጫ ነገሩን ማስተዋል እንጂ መመጻደቅ አይደለም። አለማወቅ ነውር አይደለም፤ ያለማወቅን አለማወቅ ግን ስንፍና ነው። ማንም ሰው ፍጹም አይደለም። ስህተትን ማወቅ ግን ለማደግ የሚረዳ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው። ለማደግ የምንመኝና ስለ ሥራችንም ሆነ ስለ ራሳችን የሚሰነዘሩትን አስተያየቶች በሙሉ ድፍረት ለመጋፈጥ ዝግጁ መሆን አለብን እንጂ 'እርሱን ብሎ ተቺ' ማለት የለብንም። እንዲህ እንባላለን ብለንም ከመናገርና ከመሥራት ማፈግፈግ የለብንም። ያ ሰው ያልተሳሳተ ከሆነ ለዚያ የተሳሳተ መሆኑን ለነገረው ሰው በግልጽ ሁኔታውን ማሳየት ቢችል ሰውየው ያንንም

---

[10] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፥ ገጽ 443፥ 465 እና 466።

ሰው መልሶ ያርመዋል። ስለዚህ ማንም አገልጋይ ለመፈተሽ ፈቃደኛ ሆኖ ቢገኝ ይህ የመብሰሉና ሌሎችንም ለመርዳት የመጓጓቱ ምልክት ነው። ፍጹም ማንም ሰው የለምና። ቢቻል ግን ማሔስ ከሌሎች ከመምጣቱ በፊት ከራስ ሲመነጭ፥ ስሜታዊና ኅሊናዊ ብቻ ሳይሆኑ ሚዛናዊ በሆነና በቃሉ በተመሠረተ ሁኔታ አገልግሎትና ድርጊት ሲመረመር ውብ ነገር ነው። እንዲህ ከሆነ ያልተፈጸመ ስሕተት አይፈጸምም፤ የተፈጸመም አይደገምም። ስሕተት በራስ መጥፎ ፍርድን መፍረጃ ሳይሆን መስተካከያና ሌሎች ያን ጥፋት እንዳይደግሙ መከላከያ መሆን አለበት።

በጃፓን ውስጥ የነበረ የ69 ዓመት ሽማግሌና ከ2ሺህ በላይ አባላት የነበሩት ኢቺጋኖ ሚያ የሚባለው ሃይማኖት መሥራች የነበረ ካትሱዊቼ ሞቶጊ የተባለ ሰው እንደ ነጮች አቆጣጠር ሰኔ 13 ቀን 1974 አንድ ትንቢት ተነበየ። ትንቢቱ በዚያው ሰሞን ሰኔ 19 ቀን ከጠዋቱ በ2 ሰዓት የኦሳካ ከተማ በኃይለኛ የመሬት ነውጥ እንደምትመታ ነበር። ይህ የሃይማኖት መሪ 200 ሺህ የማስጠንቀቂያ ወረቀቶችን በኦሳካና በኮቤ ከተሞች እንዲበተኑ አስደረገ። የተባለው ቀን ደረሰ፤ የመሬት መንቀጥቀጡ ግን ሳይፈጸም ቀረ። ሞቶጊም ይህ ያለመሆኑን ሲረዳ ሳሙራይ በሚባለው የጃፓን ሰይፍ ሆዱን በመቅደድ በባህላቸውና በሃይማኖቱ ሃራኪሪ የሚባለውን ግድያ በራሱ ላይ ፈጸመ። ይህ ሰው ከመሞቱ በፊት ለምን ራሱን እንደሚገድል ሲጠየቅ የሰጠው መልስ ይህን የሚያደርገው ባልተፈጸመ ትንቢቱ ሰዎችን በማወኩ ምክንያት መሆኑን ነበር። የሞቶጊ ሃይማኖት ሰይጣናዊ ሃይማኖት ነው። መሳሳቱን ማመንና መቀበል ነበረበት እንጂ ራሱን መግደሉም ስሕተት ነው። ሰው እንደመሆኑ መጠን ግን መሳሳቱን ሌላው ሳይነግረው ነው ያወቀው።

በተቃራኒው ደግሞ የራሳቸውን ስሕተት በራሳቸው ካለማወቅም አልፎ መሳታቸውን ሲነግሩአቸውና ሲያሳዩአቸውም እንኳ የማይቀበሉ አሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አማኞችን የሚያምሱና ከቃሉ ውጭ የሆኑ ነገሮችን በማስተማርና በማስደረግ የሚያስፈነግጡ ሰዎች አማኞችን ስላወኩና ከመንፈሳዊ ጉዞአቸው ስላስተጓጎሉ ጥቂት ቅር ቢላቸው እንኳ ጥሩ ነበር። ነገር ግን በቅሬታ ፈንታ እንዲህ ያሉት ሰዎች የሚያደርጉት መሳሳታቸውንና የተሳሳቱባቸውን ነገሮች የሚነግሩአቸውን ሰዎች በክፋት መመልከታቸው ነው።

ወንጌላዊ እምነት አስቀድሞ በኖረበት አካባቢ ችግር ያስከተሉና መለያየትን የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎች ከመወቀስም በላይ ቢወገዙም ማስገረም የለበትም። ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ በሒስ ከመወቀስ አልፎ መወገዝ የጀመረው አሁን ወይም በቅርቡ አይደለም፤ ቀድሞም ከተጀመረባቸው ቦታዎችና ዘመናት አንሥቶ እንደ ስሕተት ሲቆጠርና ሲወገዝ ኖሮአል። በ*መንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች* መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉት በክፍለ ዘመኑ





መጀመሪያ ዘመናዊው ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ በተጀመረበት በአሜሪካ የነበሩት እነፓርሃም ከዚህ አላመለጡም። በስሕተት ትምህርቶች አካባቢ ጥናት ያደረገ ቪንሰን ሳይናን የተባለ ጸሐፊ ይህን አስመልክቶ ሲጽፍ እንዲህ ብሎአል፥

> ምናልባት ከቀዳሚዎቹና ኃይለኞቹ ወቃሾች መካከል አንድዋ አልማ ዋይት ናት። ሲሞርንና ፓርሃምን 'የመንፈሳዊ ሰዶማዊነት መሪዎች' ያለቻቸው ዋይት በሌሎች ልሳኖች መናገራቸውን ሰይጣናዊ ልፍለፋ ብላዋለች። በዚህ ንቅናቄ ላይ የጻፈችው መጽሐፍ *አጋንንትና ልሳናት* Demons and Tongues በሚል ርዕስ በ1910 ታትሞአል።
>
> ሌላው ሰው ኤ ደብልዩ ጋድቢ ነው። በ1909 በሉስ አንጀለስ በአዙሳ ያለው የሲሞር ንቅናቄ ጋብዞት ሄዶ ሳለ እዚያ ያሉት ሰዎች በልሳን ተናግሮ ያውቅ እንደሆነ ጠየቁት። እርሱም በጥያቄአቸው በጣም ተገርሞ በላቲን ቋንቋ አንድ ጥቅስ ጠቀሰላቸው። እነርሱም ምንነቱን ሳይጠይቁት፥ 'እውነትም በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆአል' አሉ የተናገረው ልሳን መስሎአቸው። ጋድቢ በሲሞር ጉባዔና አምልኮ ጩኸትና ሥርዓት የለሽነት ተንገሽግሾ ከወጣ በኋላ፥ 'የአዙሳ ሰዎች የሰይጣን ሰባኪዎች፥ ሙታን ሳቢዎች፥ አስማተኞችና ጠንቋዮች ናቸው' ብሎአቸዋል።[11]

አንዳንዱ አደናጋሪ ልምምድ ይህን ያህል ከባድ ትችትን ለመናገር ሰዎችን ማነሣሳቱ እንግዳ ነገር አይደለም። በዚያው ዘመን ከነበሩትና እንቅስቃሴዎቹን በቅርብ ከተከታተሉት መካከል ጂ ሲ ሞርጋን ንቅናቄውን፥ 'የሰይጣን የመጨረሻው ትውከት' ሲለው፥ ዶክተር አር ኤ ቶሪ ደግሞ ንቅናቄውን፥ 'በእርግጥ ከእግዚአብሔር ያልሆነና በአንድ ሰዶማዊ የተመሠረተ' ብሎታል። ኤች ኤ አየርንሳይድ በ1912 መጽሐፉ፥ 'አስጸያፊና ግራ አጋቢ፥ ከአእምሮም የወጣ' ብሎታል። እነዚህ የተባሉት አሁን ወይም በቅርብ ሳይሆን ገና በ19 መቶዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ነው። አንዳንዶቹ ከመጠን ያለፉና የተጋነኑ ይመስሉ ይሆናል። ሆኖም በጊዜያቸው ስለተከሰተው ከገንቢ ይልቅ አፍራሽና አዋኪ የሆነ ንቅናቄ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያ ጋር የሰጡት ምላሽ ነው። ከሌላ አንፃርም ማሔሳቸውም ነው። እርግጥ ነው መጠን ባለፉት ልምምዶች ላይ የተሰነዘሩት የተጋነኑ ወቀሳዎች የችግሮቹን ጀማሪዎች ከመታረም ይልቅ ወቃሹንም ሆነ ምክሩን ከነጭራሹ እንዲጠሉት የራሱን አስተዋጽዖ ጥሎ ማለፉ አይካድም። እርማት ከኖረበት ማሔስ የፊት ለፊት ገንቢና የእርምት ትችት ነው። በአንዳንዶች ዘንድ ግሳጼ ወይም ወቀሳ ያልተለመደ ብቻ ሳይሆን የማይፈለግ በመሆኑ ስህተታቸውን መኖሪያ ሲያደርጉት ይገኛሉ።

በበርካታ የትምህርት ዘርፎች ስሕተትን መጠቆም የተከናወነ ሥራን መገምገም ነው። ጥሩው እንዲቀጥል፥ ድፍርሱ እንዲጠራ፥

---

[11] Synan, pp. 145-146.

መጥፎው እንዲቀር ማንጠሪያ ወንፊትም ነው። ዓይነተኛ ውጤትን ለማግኘትና ስሕተትን ላለመድገም ትክክለኛውም መንገድ ነው። ሰው አይሳሳትም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ስህተቱን እየደጋገመ መኖር የለበትም። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ኤሌክትሪክን የፈለሰፈው ቶማስ ኤዲሰን ነው። ኤዲሰን ብዙ እየጣረ ሳይሆንለት ቆየ። አንዱን ዘዴ ትቶ ሌላውን፥ አሁንም ሌላውን እየሞከረ ሳለ አጠገቡ የነበረ ረዳቱ ተስፋ በቆረጠ ስሜት፥ 'ተመልከት እስካሁን ከሰባት መቶ ጊዜ የበለጠ በተለያየ መንገድ ሞክረናል፤ ግን አሁንም አልሠራም' አለው። ቶማስም ተስፋ በቆረጠ ሳይሆን ተስፋ በሚሰጥ ሁኔታ መልሶ፥ 'አየህ፥ ከዚህ በኋላ እስካሁን የሠራናቸውን ሰባት መቶ ስህተቶች እንደግምም ማለት ነው' አለው። ስሕተት ከታወቀ አይደገምም።

ስሕተቱን ሌላው ካልነገረው ያ ሰው እንደምን ይታረማል? እንዲህ ያሉትን ሰዎች ለየት የሚያደርገው በቃሉ እንዳይታረሙ ቃሉን አይማሩም። የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳያርማቸውም ያንን የተሳሳተውን ነገር እንደተሳሳተ ሳይሆን እግዚአብሔር እንደነገራቸው ነው የሚመስላቸውና ያንን የሚያርም ሰውን የእግዚአብሔር ተቃዋሚ፥ የእግዚአብሔር አራሚ አድርገው ያዩታል። ብዙዎቹ ለመታረም ቀርቶ ለአርምሞ ውይይት እንኳ ፈቃደኛ አይደሉም። የአገልጋዮች የእርስ በርስ የመማማር መስመር ሁሌም ክፍትና ንጹሕ ሆኖ መጠበቅ ያለበት ነገር ነው። በሌሎች መስኮች ለፍሬያማ ዕድገት የሚውለው ይህ ስሕተትን የማሳየት ነገር በአገልግሎቶችና አገልጋዮችም ዙሪያ በንጽሕናና በቅንነት መደረግ መቻል አለበት። ይህ አንዳንድ ጊዜ የሚያሳምም ልምምድ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን፥ እንደ አካላዊ ሕመም ብንመለከተው አካላችን የመታመሙ መልእክት ለአዕምሮአችን ሲደርሰው ነው ተገቢውን ቀጣይ እርምጃ የሚወስደው። ወይም ስንታመም ወደ ሐኪም ብንሄድና መድኃኒት ቢሰጠን የመድኃኒቱ ቃና ወይም ጣዕም ጥሩ ባይሆንም ስለ ጥቅሙ ስንል ግን እንወስደዋለን።

በዚህ ውስጥ የሰይጣን ቀጥተኛና ዘዋራ የማስታበይና የማሳወር ተግባር መኖሩንም አንዘንጋ። በሰላጤው ጦርነት በኢራቅና አሜሪካ መራሹ የኅብረ ብሔሩ ጦርነት ጊዜ አንድ ነገር ተደርጎ ነበር። ጦርነቱ ከመጀመሩ ዋዜማ ምሽት ላይ አንድ ልዩ የሆነ አውሮፕላን በኢራቅ ዋና ከተማና የጦር ዕዝ ጣቢያዎች የአየር ክልል አንዣብቦ ነበር። ይህ አውሮፕላን በጣም ኃይለኛ በሆነ የኤሌክትሮኒክና ማግኔቲክ መሣሪያዎች የተሞላ ነው። አውሮፕላኑ ከላይ ሲያንዣብብ ከስሩ የሚገኙ ማናቸውንም የመገናኛ መሣሪያዎች ይበላሹና ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ። እንዲህ ከተደረገና የመገናኛ አውታሮቻቸው በሙሉ ከተበላሹ በኋላ ነበር ወረራው የተጀመረው። ሠራዊቱ ከበታች ሹማምቱ፥ ሹማምቱ ከበላይ አለቆች፥ የበላይ አለቆችና አዛዦች ከርዕሰ ብሔሩ ጋር መገናኘት





አልቻሉም። በወራሪዎቹ በኩል ግፊያው ሲፈጥን ከወዲያ ግን ቀውስና ግርግር ነበር። ግንኙነት በሌለበት ወረራ የሚፈጠረው ይህ ነው። ሰይጣንም የጊዜውን ክፋት እየነቀሰን እንዳንመካከር በሕይወታችንና በአገልግሎታችን ላይ እያንዣበበ መንፈሳዊ፥ ነገር ግን ተመሳሳይ ዘዴ ይጠቀማል።

ከአዳም ጀምሮ ከሰው ባህርያት አንዱ ጥፋትን አለመቀበል ነው። ብዙዎቻችን በወቀሳ ከመፈወስ ይልቅ በመሞካሸት እየተገበዝን ከነኩራታችን መሞትን ሳንመርጥ አንቀርም። በጊዜ ውስጥ አንዳንድ አገልጋዮች በራሳቸው አነሣሽነትም ይሁን በሌላ ረዳትነት ስሕተታቸውን አውቀው ያርማሉ። 'ተሳስቼ ነበር' ማለት ማደግና ማስተዋል እንጂ ከድጥ ወደ ማጥ መግባት አይደለም።

## "ተሳስቼ ነበር"

ይህ ቃል ወንጌላዊ ጂም ቤከር የተናገረው ምስክርነት ነው። የመሳሳቱን ሰፊ ታሪክ ለዘገበበት ከ600 ገጾች በላይ ለሆነው በፈረንጆች ቆጠራ በ1996 ለታተመው መጽሐፉ የሰጠው ርዕስም ይህንኑ ቃል፥ *I WAS WRONG* በማለት ነበር።

አሜሪካዊው ጂም ቤከር ቀድሞ 'የጤንነትና ብልጽግና ወንጌል ዋና ሰባኪ የነበረ ኋላም በመዝባሪነት፥ ማለትም፥ በእግዚአብሔር ስም ገንዘብ ሰብስቦ ለግል ጥቅም በማዋል፥ የቴሌቪዥንና ሌሎችም መገናኛ ብዙኃንን ደንቦች በመጣስ፥ እንዲሁም በዝሙት ወንጀል በመከሰስ ፍርድ ቤት ቀርቦ የ45 ዓመታት እስራት ተፈርዶበት ወደ ወኅኒ ወረደ። ከላይ ከተዘረዘሩት ንዑሳን ነጥቦች ባሻገር ዋናው የክሱ ነጥብ እምነት ማጉደሉ፥ ማለትም፥ በእርሱ ዓይነት ሥራና ሁኔታ የሚገኙ አገልጋዮች የሚጠበቅባቸውን ማኅበራዊ፥ ግብረገባዊና መንፈሳዊ ኃላፊነት ወደ ጎን መጣሉ ነው። የአርባ አምስቱ ዓመት ብያኔ በኋላ በዳግም ፍርድ ወደ አስራ አምስት ዓመት ወረደለት። ቀጥሎም በይግባኝ ወደ ስምንት ዓመት ተቀነሰለት። እንደገናም የምሕረት ልመና ተደርጎ አምስቱን ዓመት እንደጨረሰ በአመክሮ ተፈታ።

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከራሱ ሕይወትም ከጻፈው ሥራም ትልልቅ ትምህርቶች ሊገኙ ይችላሉ በሚል እምነት ስለ ጂምና ስለጻፈው መጽሐፍ በመጠኑ እንድንቃኝ እወዳለሁ። ከመጽሐፉ ውስጥ የተወሰዱት በርካታ ጥቅሶች ምናልባት አሰልቺ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል። ቢሆንም ግን ጂም በአንድ ወቅት ታዋቂ ካሪዝማዊ አገልጋይ የነበረ ሰው መሆኑ፥ ኋላም የተሳሳተባቸውን ነገሮች በግልጽና በድፍረት መናገሩ ምንጭነት ያለው ምስክርነት

ስለሚሆን አስፈላጊ በመሆኑ እንዲህ አቅርቤዋለሁ። መጽሐፉ የሕይወት ታሪኩን፥ በተለይም ለእስራት ከተዳረገበትና ወደገባበት አዘቅት ከመውደቁ በፊት የነበረውን ሕይወቱንና ትምህርቶቹን፥ እንዲሁም የወጣበትንና ስህተቱን ያስተዋለበትን ሁኔታዎች የያዘ ነው። ለመጽሐፉ የሰጠው ርዕስ ለመጽሐፍ ርዕስነት የሚመረጥ ዓይነት አይደለም። ለራሱ ለጂምም ቀላል አልነበረም። ይህን በተመለከተ እንዲህ ብሎ ነበር፥

> ተሳስቼ ነበር የሚሉት እነዚህ ቃላት ወደኔ የመጡት እንዲህ በቀላሉ አልነበረም። ከኖርኩበት ዘመን አብዛኛውን ስለ እግዚአብሔር የነበረኝ መረዳቴ ትክክለኛ ነው ብዬ አምን ነበር። ደግሞም እርሱ እኛ እንዴት መኖር እንዳለብን ያለውን ፍላጎት በትክክል ማወቅ ብቻ ሳይሆን ይህንን ሁሉም ሊያውቁት ይገባል የሚል እምነትም ነበረኝ። ይህን ለመጻፍና ለማሳተም ልቤን ከሰጠሁባቸው ምክንያቶች አንዱ እነዚያ ድርጊቶቼና አቋሜ የመነጩበት የቀድሞው የሕይወት ፍልስፍናዬ ከመሠረቱ የተሳሳተ መሆኑን ለእናንተ ለመንገር ነው። በአንድ ወቅት እንደሰበክሁት እግዚአብሔር እኛ ሁላችን ሀብታሞችና ባለጸጎች እንድንሆን ተስፋ አልሰጠንም። ወኅኒ ቤት ሳለሁ መጽሐፍ ቅዱሴን በእውነት ሳጠናው በጣም ግልጽ የሆነልኝ ነገር በውስጡ ካሉት ሰዎቹ፥ የእግዚአብሔርንም ነቢያት ጨምሮ ማለት ነው፥ የአንዳቸውም ሕይወት መከራ የለሽ አልነበረም።

> ....እኔ በመከራ የተማርኳቸው ትምህርቶች ይጠቅሙአችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ታሪኬም ለጥቂቶች የመከላከያ መድኃኒት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። እኔ የፈጸምኳቸው ስህተቶች ዛሬም በአገልግሎቶች፥ በአብያተ ክርስቲያናት፥ በሥራ ዓለም፥ በትዳርና በቤተ ሰብ ውስጥ ሳይቋረጡ እየተደገሙ ይገኛሉና።[12]

ጂም በእስር ቤት ውስጥ ሳለ በአብዛኛው ያጠና ወይም ያነብ የነበረው የኢየሱስን ሕይወት ነበር። መጽሐፍ ቅዱሱንም በአጠቃላይ በጥልቅ በማየት የተማራቸው በርካታ ነገሮች ነበሩ። ከእነዚህ አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል ጥቅስ በመንቀልና በመውሰድ ሳይሆን መጽሐፉን እንዳለና በሙሉ መቀበልን መረዳቱ ነበር። ቃሉን በጥልቅ ባጠና መጠን በዘመነኞቹ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች አካባቢ የሚነገሩት ነገሮች ከኢየሱስ ትምህርቶች ጋር መጋጨታቸው እየገባው መጣ። ቀድሞ በፒ ቲ ኤል[13] ሳለ ያስተምራቸው የነበሩትን ትምህርቶች ከጥያቄ ውስጥ ከተታቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ያስተምርበት የነበረው የአተረጓጎም ስልቱ ትክክል ያለመሆኑንም ተገነዘበ። እንደ ምሳሌ ካቀረባቸው ጉልህ

---

12 Bakker, pp. xiii-xiv.

13 ፒ ቲ ኤል Praise the Lord የሚለው ሐረግ ምኅጻረ ቃል ሆኖ ጂም የመሠረተውና ይመራው የነበረው ሄሪቲጅ ዩ ኤስ ኤ የተባለው ድርጅትና የቴሌቪዥን መረቡ መጠሪያ ስም ነው። ሄሪቲጅ ዩ ኤስ ኤ ራሱ ትንሽ ከተማ የመሰለ በርካታና የተለያዩ ሕንፃዎችን ያቀፈ ሆቴሎች፥ ሬስቶራንቶች፥ ሱቆች፥ ማረፊያ ክፍሎች፥ የስብሰባና የሴሚናር አዳራሾች፥ የአረጋውያን መጠሪያ፥ ሆስቴሎች፥ ሌሎችም በርካታ ተቋማትን የያዘ ትልቅ የመንደላቀቂያ መንደር ነበር። ፍጻሜው ግን በዕዳ ተያዥነት መወረስ ሆነ።





ነጥቦች አንዱ ኢየሱስ በምድረ በዳ ሲፈተን ከጠቀሳቸው ጥቅሶች አንዱ፥ ‘ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም’ የሚለው ነው።

> ....ይህን ጥቅስ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ፤ ጠቅሼዋለሁ፤ ሰብኬዋለሁ። ነገር ግን በእስር ቤት ሳለሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ‘ሁሉ’ የሚለው ቃል ከገጹ ውስጥ ዘልሎ የወጣ ያህል ወደ ውስጤ የገባ መሰለኝ።

> ለዓመታት በእግዚአብሔር ቃል መመራትን ሳስተምር ....በአንድ ጥቅስ ወይም በተወሰነ ክፍል ብቻ አተኩር ነበር። አንድ ጥቅስ ከዚህ አንድ ጥቅስ ከዚያ እየወሰድኩ መጽሐፍ ቅዱስን እግዚአብሔር ከሚፈልገው ይልቅ እኔ የምፈልገውን እንዲናገር ወደማድረግ ወጥመድ ገብቼ እንደነበር አስተዋልኩ።[14]

ማንኛውም ሰው ወደ እስር ቤት ሲገባ በእጁ የሚኖረው ትልቅ ንብረት ጊዜው ነው። ጂም ይህን ጊዜውን ዘላቂ ትርፍ ለሚሰጥ ለቃሉ ጥናት አውሎት ነበር። ሲከተላቸውና ሲያስተምራቸው የኖረውን ልምምዶች ስሕተት ያስተዋለውና ያለፈውን የአገልግሎት ዘመኑን የገመገመው በዚህ ጊዜ ነበር። ማቴ. 7ን ሲያጠና በቁጥር 15-19 የተጻፈውን የበግና ተኩላ ምሳሌነት እንዴት እንደተረዳ ሲጽፍ፥

> ቀድሞ እረዳ የነበረው ሐሰተኞች ነቢያት በዮሐንስ ራእይ እንደተጻፈው አውሬ ፀረ ክርስቶስ የሆኑ መልእክቶችን በድፍረት የሚሰብኩና እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ፥ ‘አሃ፥ ያ ሐሰተኛ ነቢይ ነው’ ብለን በቀላሉ እንደምንለያቸው ነበር። እዚህ ግን እግዚአብሔር እያሳየኝ ያለው ሐሰተኛ ነቢያት የማይጎዱና ሰላማዊ፥ እንዲሁም ድምፃቸውም ሆነ መልካቸው በእግዚአብሔር በረት ያሉ በጎችን መስለው የሚቀርቡ በእርግጥ ግን በውስጣቸው ነጣቂ ተኩላዎች እንደሆኑ ነው።[15]

በዚያው ክፍል ሰዎችን ከፍሬያቸው ማወቅን ስለተማረበት አጋጣሚም ይመሰክራል። ሰዎችን በፍሬያቸው ሳይሆን በሥራቸውና በሥራቸው ውጤት ሲገመግም መኖሩን ይናገርና እግዚአብሔር ግን በሥራችን ያለመደነቁን እንደተረዳ ጽፎአል። ይልቁንም በሰዎችና በራሱም ውስጥ ሊፈልጋቸው የተገቡት በገላ. 5፥22-23 የተጻፉት የመንፈስ ፍሬ እንደነበሩ ተረዳ።

> እግዚአብሔር እያሳየኝ የነበረው ሰዎችን መመዘን ያለብኝ በድርጊታቸው፥ በቃላቸው፥ በሥራቸው፥ ወይም በችሎታቸው ሳይሆን በመንፈሳዊ ፍሬያቸው እንዲሆን ነበር። በፒ ቲ ኤል መሪ ሳለሁ ከፈጸምኳቸው ስህተቶች አንዱ ተሰጥዖዎች፥ ችሎታዎችና ስጦታዎች ባሉአቸው ሰዎች በቀላሉ በአድናቆት መሳቤና በቀላሉ መወሰዴ ነው። እነዚህ ሰዎች ሕይወታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን ሲመዘን እንደቃሉ እየኖሩ ያለመሆናቸውን ልቡናዬ እያወቀው፥ ግን ትልልቅ ሰባኪዎች፥

---

14 Bakker, pp. 329-30.

15 Ibid., pp. 460-1.

> አስተማሪዎች፥ ዘማሪዎች፥ ሙዚቀኞች ወይም እንዲህ ያሉት ስጦታዎች ስላሉአቸው እገረምባቸው አደንቃቸው ነበር።[16]

ጂም በመሪነቱ ዘመናት በዙሪያው ካሉት ሰዎች አንዳንዶች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ችግር እንዳለባቸው እያወቀም ዝም ይላቸው ነበር። ስለዚህና ይህንንም ለምን ያደርግ እንደነበር ሲጽፍ፥ "አንዳንዴ በአገልግሎታችን ወይም በቢሮ ሠራተኞቻችን ዘንድ በሕይወታቸው ፈቅደው የደበቁት ኃጢአት ያለባቸው ሰዎች እንዳሉ አውቅ ነበር። ለጸጋ ስጦታቸው ስል ግን በኃጢአቶቻቸው ላይ ዐይኖቼን እጨፍን ነበር። በማሳሰብና በመገሰጽም ፈንታ እንዲቀጥሉ እተዋቸው ነበር። ምናልባት ጣታቸውን በራሴ ላይ እንዳይጠቁሙም በመፍራት ይሆናል፤ ምንም ቢሆን ግን ተሳስቼ ነበር።"[17] ጂም ይታለል የነበረው በሚታዩት ምልክቶችና ውጤቶች፥ ማለትም በፈውስና በመሳሰሉት ነገሮች ነበር። እነዚህንም ነገሮች ራሳቸውን፥ ማለትም፥ ሰዎቹ ከመስመር የወጡ ሆነው ውጤቶቹ ግን እንደዚያ የሆኑበትን ነገር እንዴት እንደተረዳ ሲጽፍ እንዲህ ይላል፥

> ሙሉ በሙሉ ባልረዳም ያወቅኩት አንድ ነገር ግን አለ፤ ያም በአንድ በኩል ስለ እግዚአብሔር መስበክ፥ ሙዚቃ መጫወት፥ መዘመር፥ በስሙ ተአምራት ማድረግና በሌላ በኩል ደግሞ ከእርሱ መንገድ ፈጽሞ በወጣ ሁኔታ መገኘት መቻሉን ነው። እንደኔ መረዳት ይህ የሚሆንባቸው ምክንያቶች ሁለት ናቸው፤ የመጀመሪያው፥ የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪ ከተሰጡ በኋላ ተመልሰው የማይወሰዱ መሆናቸው ነው፤ ሮሜ. 11፥29። ምንም እንኳ ያለጥበብ ብንጠቀምባቸውና ከእርሱ ክብር ይልቅ ለራሳችን ጥቅም ብናውላቸውም እግዚአብሔር የጸጋ ስጦታዎቹን መልሶ አይወስድም። ሆኖም ስጦታ ኖሮት ልቡ ግን ከእግዚአብሔር በራቀ ሰው የሚፈጸመው ክፋትና አደጋ እጅግ ትልቅ ነው። ሁለተኛው ምክንያት፥ እግዚአብሔር የራሱን ቃልና የሕዝቡን እምነት ማክበሩ ነው። ለዚህ ነው መልእክቱን የሚያመጣው አገልጋይ ወይም ዘማሪ የተበላሸ ቢሆንም እንኳ ሰዎች የሚድኑት፥ የሚባረኩት፥ የሚፈወሱት።[18]

ሌላው ስህተቱ እንደሆነ ጂም የጠቆመው ነገር የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት ከመገንባት ይልቅ ታዋቂ የቴሌቪዥን መረብ፥ ትልቅ ዝና ያለው አገልግሎትና ታላላቅ ሕንፃዎችን መገንባቱን ነበር። በጊዜው በነበሩ አንዳንድ ሰዎች ይህ ተግባሩና ዝንባሌው ትክክል ያለመሆኑ ቢነገረውም አልሰማም። በነዚህ ነገሮች መጠመዱ በቀጥታ ከሰዎች ጋር ለመሆን ወይም ጊዜውን በሰዎች ላይ ለማጥፋት፥ ለመጸለይ፥ ቃሉን በጥልቀት ለማጥናት ጊዜ ሊሰጠው አልቻለም። ጂም ፒ ቲ ኤልን እንደገና መሥርቶ የማገልገል ዕድል ቢገጥመው ከበፊቱ የተለየ የሚያደርገው ነገር ምን እንደሆነ

---

[16] Ibid. pp. 461.
[17] Ibid. pp. 461.
[18] Ibid. pp. 470.





ተጠይቆ የሰጠው መልስ፥ ጊዜውን የሚታይ አካላዊ መዋቅር ላይ በማባከን ሳይሆን ሰዎች ከኢየሱስ ጋር በፍቅር እንዲጠመዱ እንደሚጥር ነበር። የራሱን የሄሪቲጅ ዩ ኤስ ኤ ሥራዎችና የኢየሱስን ጸጋ እንደ ስጦታ መጠቅለያና እንደ ስጦታ አነጻጽሮታል። እንደገና አጋጣሚ ቢያገኝ የሚያደርገው ነገር ጉዳዩ ከስጦታ መጠቅለያው ጋር ሳይሆን ከስጦታው ከራሱ ጋር እንደሚሆንና ዐይኖቹንም ከሚታዩ ምድራዊ ነገሮች ላይ አንሥቶ በኢየሱስ ላይ ይተክል እንደነበር ጽፎአል።

የመጽሐፉ አንዱ ንዑስ ርዕስ እንደ ዋናው ርዕስ ተሳስቼ ነበር የሚል ነው። በዚህ ክፍል ስለ ሁለት ነገሮች ይዘረዝራል፤ የመጀመሪያው 'የብልጽግና ወንጌል' ስለሚባለው ነገር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዐውደ ወጥ ስለሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ነው። የብልጽግና ትምህርቱ የተሳሳተ መሆኑን ያስረዱት ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ ያስተማራቸውን ትምህርቶች ናቸው።

> በይግባኝ ስሚው ጊዜዬ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን የኢየሱስን ትምህርቶች ጥናቴን ጨርሼ ነበር። ለብዙ ወራት ኢየሱስን ካጠናሁ በኋላ ያስደነቀኝ ድምዳሜ ኢየሱስ ስለ ገንዘብ አንድም መልካም ነገር ያለመናገሩ ነው። ኢየሱስ ስለ ሀብት፥ ስለ ብልጽግናና ስለ ምድራዊ ጥቅም የተናገራቸው ነገሮች በሙሉ አሉታዊ ናቸው። ስለ አባካኙ ልጅ ሳጠናም ስጠኝ ስጠኝ ማለት ወደ እሪያ ጋጣ የመሄጃው አቋራጭ መንገድ መሆኑን ነው የተረዳሁት። ወደ ወኅኒ ቤት የመግቢያው መንገድም ብዙ ጊዜ የሚጀምረው በዚሁ ቃል ነው። ...ስለ ገንዘብ የሚናገሩት የኢየሱስ እውነተኛ ቃላት ልቤንና አእምሮዬን ሲመቱት ሰውነቴ ቀፈፈኝ። ተሳስቼ ነበር። በእውነት ተሳስቼ ነበር። ይልቁንም የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት እረዳበት የነበረበት መንገዴ የተሳሳተ ነበር። ስሕተተኛ ብቻ አልነበርኩም፤ እንዲያውም የኢየሱስን ትምህርት ተቃራኒ አስተምር ነበር። ክርስቶስን እየተቃረንኩ እንደነበር ሳስበው ደነገጥኩ፤ ልቤንም የሰበረው ይህ ነበር።[19]

በፒ ቲ ኤል በነበረ ጊዜ ክርስቲያኖች የሐዋርያትን ጸሎት ሲጸልዩ፥ 'ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን' እንዳይሉ፥ እንዲሁም ስለ ጤንነትና ስለ ብልጽግና ሲጸልዩ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚል ነገር እንዳይናገሩ አስተምሮአል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ብልጽግናችንና ጤንነታችን ነው ብሎ ያምን ነበር። ስለዚህ ነገር እንደፈቃድህ ብሎ መጸለይ እምነት ማጣትና መጠራጠር ነው ብሎ ያምንና ያሳምንም ነበር። አሁን ግን ስለዚህ ነገር ሲጽፍ፥ "እንዴት ያለ ትዕቢት፥ እንዴት ያለ ሞኝነት፥ እንዴትስ ያለ ኃጢአት ነበር! መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ላይ ግምታዊ እምነት እንዳናደርግና

---

[19] Ibid. 531-2.

‘እግዚአብሔር ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን’ ያዕ. 4፥15 እንድንል ያስተምረናል” ብሎአል።[20]

እንዲህ ያሉ ስህተቶችን የሚያስተ፦ሩ አስተማሪዎች ከባህርይ ሌላ የአተረጓጎም ስሕተት የተጠናወታቸው ናቸው። አንድን ነጠላ ቃል ወይም ሐረግ ወይም ጥቅስ ከግንዱ ወም ከዐውዱ ገንጥለው ያስተምራሉ። ጂምም በቀድሞው የአገልግሎት ዘመኑ በዚህ የተካነ የጥቅስ ጠምዛዥ እንደነበር፥ እነ ዘዳ. 8፥18፤ ሉቃ. 6፥24፤ ዮሐ. 10፥10፤ 3ዮሐ. 2፤ እና የመሳሰሉትን ጥቅሶች እንዴት ያላሉትን እንዲሉ ያሰኛቸው እንደነበር ተናግሮአል። እነዚህን ስህተቶቹን በእስር ቤት ከነበሩ ክርስቲያን ጓደኞቹ ጋር በነበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜያቸው በሰፊው ተነጋግረውበታል። ቀደም ሲል ይህንን ላስተማራቸው ሰዎች ሊደርሳቸው በሚችል ሁኔታ ትክክለኛ ያልሆነ ትምህርት አስተምሮአቸው እንደነበርና የብልጽግና ትምህርቱም የተሳሳተ መሆኑን የሚገልጥ ግልጽ ደብዳቤ ጽፎ ይቅርታ ጠይቆአቸዋል። ዳብዳቤው በከፊል እንዲህ ይላል፥

> በአገልግሎቴ ስር ተቀምጣችሁ የተማራችሁትን ሁሉ በምድራዊ ብልጽግና ላይ ያተኮረ ወንጌል በመስበኬ ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እጠይቃለሁ።
>
> ...ዛሬ ብዙዎች የእግዚአብሔር በረከት በእነርሱ ላይ የመኖሩ ምልክት አድርገው የሚወስዱት አዲስ መኪና፥ ቤት፥ ጥሩ ሥራ፥ የመሳሰሉትን ነው። ነገር ግን ይህ ከእግዚአብሔር እውነት የራቀ ነው። ይህ እውነት ከሆነ የሃሺሽና የቁማር ባለቤቶችና የፊልም ኮከብ ተዋንያን በእግዚአብሔር የተባረኩ ናቸው ማለት ነው። ኢየሱስ ብልጽግና የእግዚአብሔር በረከት ምልክት መሆኑን አላስተማረም። እንዲያውም ኢየሱስ ያለው ለባለጸጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ከባድ መሆኑንና ብልጽግና አታላይ ነገር መሆኑን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ምክር እንዳለ ከተቀበልን የቁሳዊ ነገሮችን ብልጽግና እንደ እግዚአብሔር በረከት ምልክት እንድናደርግ የሚያሳይ ትምህርት የለም።
>
> ኢየሱስ ያለው ወደ ሕይወት የምትወስደው መንገድ የቀጠነችና የሚያገኟትም ጥቂቶች መሆናቸውን ነው። ዛሬ ከመድረኮች የሚቀርበው ጥሪ፥ ‘ደስታንና ጥሩ ነገሮችን፥ ቤትንና መኪናን፥ ምድራዊ ሀብትንና የመሳሰሉትን የሚፈልግ ማን ነው?’ የሚል ሳይሆን፥ ‘ወደዚህ መጥቶ ክርስቶስንና የመከራውን ኅብረት ለመካፈል የሚወድ ማን ነው?’ የሚል ነው መሆን ያለበት። ኢየሱስ የጠራን እውነተኛ ሕይወትን ሊሰጠን ሲሆን ይህም ለዓለምና ለራሳችን በመሞት ነው።[21]

ይህ ደብዳቤ ስንቶቹን ስለመለወጡ የሚታወቅ ነገር የለም። እርሱ ግን ለማረም ማድረግ የነበረበትን አድርጎአል።

[20] Ibid. 532.
[21] Ibid. 540-1.





ሰዎች የመድረክና የአደባባይ ሰዎች ሲሆኑ የግልነታቸው ወይም የራሳቸው መሆናቸው ይቀርና የሕዝብና የጉባዔ ንብረት ይሆናሉ። ይህ በአንድ በኩል ትክክለኛ ባይሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ሊያመልጡት የማይችሉት ነገር ነው። ለመሆን ባይፈልጉም አለመሆን አይችሉም። እንዲህ ከሆኑ መልካም ይዞታቸውን ለመጠበቅ ሲሉ አምባ ገነን ካልሆኑ በስተቀር ለሌሎች አስተያየትም ሆነ ለትችት ግልጥ መሆን አለባቸው። ‘ማንም ሊና ገረኝ አይገባም’ የሚሉ ከሆኑ ቀድሞውኑ ወደዚያ መውጣት አይገባቸውም። ትልልቅ ሰዎች የሚሠሩት ጥፋት ያለ ልክ ይጋነና ል። ጥፋቱ ትልቅ ባይሆንም እንኳ ሰዎቹ ታዋቂዎች ናቸው። ጥፋታቸውም ከተርታው ሰው ተመሳሳይ እንከን ይልቅ ይገናል። ለምሳሌ፥ ይህ እዚህ የተጠቀሰው ጂም፥ የአሜሪካው ፕሬዚደንት ክሊንተን፥ የእንግሊዝዋ ልዕልት ዳያና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሰዎች ለጥቂት ዓመታት የጋዜጠኞች ቀስቶች ዒላማዎች ሆነው ቆይተዋል። እንደዚያ በነበሩባቸው ጊዜያት እነርሱ የፈጸሙትን የመሰሉ ጥፋቶች ብዙዎች አንዴ አይደለም ደጋግመው ፈጽመውታል። ግን ማንም ጋዜጠኛ አልዘለዘላቸውም። እኒህ ግን በብዙዎች ዘንድ እንደ ናሙና የሚታዩ ናቸውና ቁስሉ ይጠና ባቸዋል፤ እየቆየም ያመረቅዝባቸዋል። አንዳንዴም ይቅርታም ከተደረገላቸው በኋላ እንኳ ከታሪካቸው ውስጥ ጠባሳው ፈጽሞ አይሽርም። እነርሱ ራሳቸው ቢረሱትም እንኳ በአንድ ወቅት ሲከተላቸውና ሲያደንቃቸው የኖረው ተራው ሕዝብ አይረሳውም። አገልጋዮችም እንዲሁ ናቸው።

ጂም በአሁኑ ጊዜ ፍሬያማና በብዙዎች ዘንድ የተወደደ አገልግሎትን እያገለገለ የሚገኝ ሰው ሆኖአል። አንዳንዴ መሪዎች ራሳቸው ‘ተሳስቻለሁ’ ቢሉም ይከተላቸው የነበረው ጎራ ቀድሞ በቀደዱለትና ባሳዩት መንገድ ከመገስገስ የማይመለስበት ሁኔታም ይኖራል። በቶሮንቶ ኤርፖርት ቪኒያርድ ቤተ ክርስቲያን ተጀምሮ ስለነበረው የቶሮንቶው በረከት ወይም ቅዱስ ሳቅ ስለሚባለው የስሕተት ልምምድ የቪኒያርድ ቤተ ክርስቲያን ቆርቋሪ የነበረው ጆን ዊምበር ስለጉዳዩ ለአብያተ ክርስቲያናቱ ቦርድ የዘገባ ምላሽ እንዲያቀርብ ተጠይቆ እንዲህ ያሉ አዳዲስ ክስተቶች እንዳይከለከሉ፥ ነገር ግን እንዳይበረታቱና አደባባይ ላደባባይ እንዲታዩ እንዳይደረጉ ጽፎላቸዋል። ይህ በፈረንጆች በ1994 ነው። በቀጣዩ ዓመት ደግሞ ለቪኒያርድ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንዲህ ብሎ ነበር፥

> በማናቸውም ጊዜ፥ በቶሮንቶም ሆነ በሌሎች ቦታዎች የሚታዩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ ምንም ዓይነት እንግዳ ልምምዶችን ከቶ አንደግፍም፤ አናበረታታምም፤ እንዲሁም ስነ መለኮታዊ የማጽደቂያ ቃልም ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ አናቀርብላቸውም። ደግሞም እነዚህ ልምምዶች

> የእውነተኛ መንፈሳዊነትም ሆነ የእውነተኛ መነቃቃት ምልክት ሆነው ሊቀርቡ አይችሉም።[22]

ራሱ የቪኒያርድ አብያተ ክርስቲያናት ቆርቋሪ እንዲያ ማለቱ ግን ልምምዱን አላከሰመውም። አንድ ቦታ ሲጠፋ ከጠፋበት የተጫረው እሳት ሌላ ቦታ መለኮሱና መንደዱም አይቀርም።

አንዳንዴም ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ ሲብስ ይታያል። ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው የሚለራውያን እንቅስቃሴ የጅማሬ ዘመናት ናቸው። የዛሬ 150 ዓመታት ግድም በኋላ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት የተባሉት ቀድሞ በጀማሪው በዊልያም ሚለር ስም ሚለራውያን ወይም Millerites እየተባሉ ነበር የሚጠሩት። በነበሩበት በኒው ዮርክ በዘመኑ የነበሩ አንዳንድ አስተማሪዎች ከትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 8 እና 9 በመነሣት የዘመኑንም ቁጥር 2300 ዓመታት በማድረግ ክርስቶስ የሚመጣው በ1843 እንደሆነ አስልተው ገመቱ።

ሚለር ክርስቶስ በዚህ ጊዜ ይመጣል ብሎ በ1840ዎቹ መጀመሪያዎቹ ዓመታት አንድ ቀን ወሰነ። ይህ ትምህርቱም ተጋንኖ ተወራና ብዙ ተከታዮችን አፈራ። የተባለውን ቀን መጣና ሄደ፤ ክርስቶስ ግን አልመጣም። ሌላ ቀን ቀጠረ። አሁንም ክርስቶስ አልመጣም። ከዚያ በኋላ እንደገና ሌላ አንድ ብቻ ሳይሆን ሌሎች በርካታ ቀኖች ተቀጠሩ። ሁሉም ከሸፉ።

ስህተቱን ተረድቶ ዊልያም ሚለር ቀነ ቀጠሮ መስጠት አደገኛ ስሕተት መሆኑን ቶሎ ብሎ ነበር ያወቀው፥ የተጸጸተና የተመለሰውም። ‘ስህተቴን እናዘዛለሁ፤ ቅሬታዬንም አልደብቅም። ሆኖም የጌታ ቀን በቅርብ፥ እርሱም በደጅ መሆኑን አምናለሁ፤ ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ የጌታ ቀን በድንገት እንዳይመጣባችሁ ነቅታችሁ እንድትጠብቁ እመክራችኋለሁ’ ማለቱ ተጽፎአል።[23] እርሱ መሳሳቱን አምኖ ቢናገርም ይከተሉት ከነበሩት አንዳንዱ ገፍተው ሄዱ። ጄምስ እና ባለቤቱ ኤለን ዋይት ከሌሎች ሰዎች ጋር አንድ ቡድን ሆነው በትምህርቱ ቀጠሉ። የተቀጠሩት ቀኖች ሳይሠሩ ሲቀሩ ክርስቶስ ወደ ምድር ሳይሆን ወደ ሰማያዊቱ ድንኳን እንደ ሙሽራ ሆኖ መምጣቱን፥ የምሕረት በር መዘጋቱን፥ ሰባተኛው መለከት መነፋቱን፥ ስለ ሰባተኛ ቀንና ሌሎችንም አዳዲስ ትምህርቶችን ጨምረው ቀድሞ በተተለመው ፈር የራሳቸውን መንገድ ቀይሰው መንጎድ ጀመሩ። ራሱ ቀድሞ የሚለር ተከታይ የነበረና ኋላም በመጀመሪያዋ የነጄምስና ኤለን ዋይት ቤተ ክርስቲያን ለ28 ዓመታት ሲያገለግል ቆይቶ የስሕተት ትምህርቶቹን ተረድቶ የወጣ ዲ ኤም ካንራይት የተባለ ሰው

---

[22] Synan, 277.
[23] Martin, p.521





ሚለር ስህተቱን ስለመረዳቱ በሰፊው ጽፎአል። ካንራይት ሚለርን ራሱን በመጥቀስ፥

> ባለፉት በጉልህ ይታዩ በነበሩት ዓመታቴ የተሰሙኝን ቅሬታዎች በግልጽ አሳውቃለሁ። በዚያን ጊዜ የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት ጠብቀን ነበር። ዛሬ ግን፥ ያኔ አልተሳሳትንም ነበር ማለት ታማኝ ያለመሆን ነው። ስሕተቶቻችንን በግልጽ ለመናዘዝ ማፈር የለብንም። ኢየሱስ እንደ ሙሽራ ሆኖ ያኔ መጥቶአል፥ የምሕረት በር ተዘግቶአል፥ ለኃጢአተኞች ደኅንነት አብቅቶአል፥ ሰባተኛው መለከት ተነፍቶአል የሚባሉትን አዳዲስ ንድፈ አሳቦች አላምንባቸውም።[24]

የዊልያም ሚለር ተሳስቻለሁ ማለት አንዳንዶችን ቢያበሳጭም፥ አንዳንዶችን ግራ ቢያጋባም፥ የመጀመሪያ ትምህርቱን የሰሙና የተከተሉትን ሁሉ ሊያርም ባይችልም ማስተዋል ለሚችሉት ከስሕተት ለመመለስ መንገድ ከፍቶላቸዋል። ‘ተሳስቼ ነበር’ ወይም ‘ተሳስቻለሁ’ ማለት ነውር አይደለም።

የስሕተት ተቀባይነት ከምዕመናን ይልቅ በመሪዎች ከሆነ ክፋቱ የባሰ ነው። አስተዋይ ምዕመናን ሊያርሙ ይሞክራሉ፥ ድምፃቸው የሚሰማውን ያህል ለማስጠንቀቅ ይጮኻሉ፥ የሚሰማ ሰምቶ ይጠነቀቃል። ነገሩ ከጠነከረና መታገስ ካቃታቸው ቢበዛ የሚያደርጉት ወደ ሌላ ጤናማ አምልኮና ትምህርት ወዳለበት መሄድ ነው። የመሪዎች ድምፅ ግን ጎልቶ ይሰማል፥ ይደመጣልም። ስለዚህ መሪዎች ስሕተትን በዝምታ ማስተናገድ ከቶ የለበቸውም። የሳቱ አገልጋዮችም መሳታቸውን መቀበልን እንደ ወንጀል ማየት የለባቸውም። በእርግጥ፥ ተሳስቼ ነበር’ ወይም ‘ተሳስቻለሁ’ ማለት ነውር አይደለም።

## ተቀባይነት ያገኙ ስሕተቶች

አንዳንድ ስህተቶች በግልጽ ይታያሉ፥ ይታወቃሉ፤ ሰዎችም ጥንቃቄ ያደርጉባቸዋል። አንዳንዶች ግን ስሕተት ሆነው ሳለ ስሕተት ሳይመስሉ ተቀባይነት ያገኛሉ። እነዚህ ተቀባይነት የሚያገኙ ስህተቶች ካላገኙቱ ይልቅ አወናባጅ ባህርይ አላቸው። ብዙ ከመቆየትና ከመደመጥ የተነሣ እነዚህ ስህተቶችና ልምምዶች ወደ ብዙዎች ጉያ እንዳይወጡ ሆነው ገብተዋል። አሳቾቹም ይሁንታን የተቸሩ አዋኪዎች ሆነዋል። አዋኪዎች፥ ግን ተቀባይነትን የተጎናጸፉ አዋኪዎች።

እነዚህ ተቀባይነት ያገኙ ስህተቶች ልክ እንደትሮይ ፈረስ ያሉ አደገኛ ነገሮች ናቸው። የትሮይ ፈረስ በጣም የሚታወቅ ታሪክ

---

[24] Canright, 77

ነው። ታሪኩ እንዲህ ነው። በጥንትዋ ግሪክ አገር የነበሩ የትሮይና የእስፓርታ ሰዎች ጠበኞች ነበሩ። የትሮይ ንጉሥ የእስፓርታውን ንጉሥ ሚስት ሔለንን አሳፍኖ ይወስዳታል። ትንንሾቹ የግሪክ መንግሥታትም ኅብረት በመፍጠር ትሮይን ለመደምሰስና የንጉሡን ሚስት ለመመለስ ቃል ተገባብተውና ተማምለው ጦርነት ይጀምራሉ። ጦርነቱን ማንም ሳያሸንፍ በግንብ ተከብባ ከተመሸገችው የትሮይ ከተማ ውጭ እየተዋጉ ለዓመታት ቆዩ።

ከዚህ በኋላ ዩሊሲስ የተባለው ብልሃተኛ ሰው ወደ ከተማዋ የሚገቡበትን መንገድ አቅዶ አሳወቃቸው። በዘዴውም ተስማሙ። በጣም ትልቅ የእንጨት ፈረስ ከሠሩ በኋላ ይህ ግዙፍ ቅርጽ ለከተማዋ ሴት አምላክ ለአቴና የተበረከተ ስጦታ መሆኑን አስወርተው ወደ መርከቦቻቸው እየገቡ ወደ አገራቸው መመለስ ጀመሩ።

ምንም ጥርጣሬ ያልገባቸው የትሮይ ሰዎች የወራሪዎቹን መመለስ በሚገባ ካረጋገጡ በኋላ ትልቁን የከተማዋን በር ከፍተው የእንጨት ፈረሱን ለማየትና ከዚያም ወደ አደባባያቸው ለማስገባት ሄዱ። ዙሪያውን እየዞሩ በአንክሮ ከተመለከቱት በኋላ ምንም ተንኮል የሌለበት የእንጨት ፈረስ ብቻ መሆኑን አረጋግጠው እየጎተቱ ማስገባት ጀመሩ። ባሰናዱለት አደባባይ ካቆሙት በኋላ የደስታ በዓል ማክበር ጀመሩ። ቀኑ ከመሸ በኋላ የትሮይ ሰዎች ለማረፍ ወደየቤታቸው ሲሄዱ ወደ መርከቦቻቸው ገብተው የተመለሱ የመሰሉት እስፓርታውያን ደግሞ መርከቦቻቸውን አዙረው መመለስ ጀመሩ። እኩል ሌሊት ሲሆንም በጸጥታ ወደ ትሮይ ዋና በር ተጠጉ። በዚያኑ ጊዜ ደግሞ በፈረሱ ውስጥ የነበሩት የተመረጡ ወታደሮች በፈረሱ ሆድ ጎን የተሠራውን በር በመክፈት በገመድ ተንጠላጥለው ወርደው ዋናውን በር በመክፈት ወራሪዎቹ ወደ ትሮይ እንዲገቡ አደረጉ። እንዲህ ከገቡ በኋላ የእስፓርታ ሰዎች የትሮይን ሰዎች ፈጅተውና ሔለንን በእጅ አድርገው፥ ከተማዋንም አቃጥለው ከአሥር ዓመታት በኋላ ወደመጡበት አገራቸው ተመለሱ።

ቤተ ክርስቲያን እንዲህ የመሰሉ የእንጨት ፈረሶች ወደ ውስጥዋ መግባታቸውን ያስተዋለች አትመስልም። ጥሩና ለስላሳ ቅርጽ ስላላቸው ለጊዜው ሳይቆረቁሩ እጉያዋ መግባታቸው ባይታወቃትም በፈረሶቹ ውስጥ ያሉት ነገሮች ቆይተው የሚያቃጥሉና የሚያፈራርሱ ናቸው። እነዚህ በጥሩ ቃላትና አዳዲስ የአቀራረብ ሽፋን የሸበረቁ አሞሌ እያላሱ ወደ ቄራ የሚወስዱ አራጆችና በላኞች ናቸው። የትሮይን ፈረስ እንደ ስጦታ ፈረስ ብቻ አይተው ወደ አደባባያቸው ያስገቡት ተጎድተውበታል። መልካም የመሰሉንንና ተቀባይነትን የተላበሱ ልምምዶች ወይም አስተያየቶች የለምንም ፍተሻ መቀበል የሚያመጣው ችግር በቀላሉ የሚሻር አይሆንም። ቀጥሎ የምናያቸው ጥቂቶች ናቸው። እነዚህን





የሚመስሉ ሌሎች በርካታ መኖራቸው ግልጽ ነው። እነዚህንም ሆነ የሚመስሉአቸውንም ሁሉ ጠንቅቀን ልናይ ያሻል።

ሀ፥ 'ይህ የነ...ቤተ ክርስቲያን ዶክትሪን ነው።'

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚናገራቸውን ነገሮች ለመሸሽ ይህ የእገሌ ያ ደግሞ የእገሌ ትምህርት ማለት አደገኛ ነው። የትኛውንም ትምህርት የእገሌ ወይም የነእገሌ ከማለት ይልቅ፥ 'ይህ ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው ወይስ አይደለም?' ብሎ መጠየቅ ትክክለኛው አቀራረብ ነው። ማንም አማኝ የሚያመልክባት ቤተ ክርስቲያን ያላትን የእምነት አቋምና ግልጽ ባልሆኑ አጠያያቂ ትምህርቶች ላይ ያላትን አመለካከት ማወቅ ይገባዋል። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናትና መሪዎች በእንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ላይ ግልጽ አቋምን በማሳየትና ተገቢውን ትምህርት በመስጠት ፈንታ፥ 'እኛ እንደዚህ እናምናለን፥ እነርሱ ደግሞ እንደዚህ ያስተምራሉ' በሚል ሽፋን ከእውነት ጋር መጋፈጥን ይሸሹታል። አንዳንዶች ደግሞ በደፈናው ዶክትሪን የሚባለውን ነገር ይጠሉታል። ዶክትሪን ማለት ትምህርት ማለት ነው። ቃሉ ደግሞ ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ ይላል፤ 1ጢሞ. 4፥16። መጠየቅ ያለብን ይህ ትምህርት በቃሉ የተደገፈ ወይም ያልተደገፈ መሆኑን ነው።

ለ፥ 'ይህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ነው።'

ምናልባት ብዙ አስተማሪዎች ይህን ቃል ከመድረኮች ሲናገሩት ሰምተን ይሆናል። ለመሆኑ መቼ ነው አንድ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን የሆነውና ሌላው ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ሳይሆን የቀረው? መለኪያውስ ምንድርነው? ይህኛውን ዘመን ካለፈው ልዩ ያደረገው ነገር በትክክል ካለ ያ ነገር ምንድርነው? ይህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ከሆነ የአብ ወይም የወልድ አይደለም ማለት ነው? ወይም ወልድና መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ዘመን አልነበሩም፥ አልሠሩም ልንል ነው። ዘመናትን እንደዚያ እንድንከፋፍል፥ ማለትም፥ የአብ ዘመን፥ የወልድ ዘመን እንድንል የሚያስደፍረን መነሻችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው ወይስ ሌላ? በቃሉ ውስጥ ዘመናት ለሥላሴ ተከፋፍለው አናገኝም። ይህን ዘመን ከቃሉ አንፃር ከመረመርነው ግን ይልቅስ ይህ ዘመን የመጨረሻው ዘመን ሆኖ ነው የምናገኘው። በመጨረሻው ዘመን ደግሞ እጅግ አብዝቶ የሚሠራው የትኛው መንፈስ መሆኑ በግልጽ ተጽፎአል።

ሐ፥ 'አልደረሱበትም፤ እውነቱ ሲገባቸው ይረዱታል።'

ይህ ራስንና የራስን ልምምድ እጅግ ከፍ አድርጎ የመመጻደቂያ በዚያ ልምምድ ውስጥ የሌሉትን ሁሉ ደግሞ የሚያንኳስስ አነጋገር ነው። ለጠባብና ግላዊ ልምምድም ሰፊ በር የሚከፍት አባባል ነው። በእርግጥ ሳይገባቸው ብዙ የሚያጠፉ ሰዎች ከየማእዘናቱ መኖራቸው እውነት ነው። ሆኖም በመጀመሪያ ሳይስተዋል የተገባበትን የራስን ሁኔታ ከቃሉ አንፃር ላለማየትና ከታየም ስሕተትን ላለመቀበል ሲባል በሌላው ያለማወቅና ያለመረዳት ሰበብ ስር መደበቅ ከእውነት መሸሽ ነው። ደግሞም ልምምድን ከቃሉ አብልጦ ማየት የሚያመጣው መዘዝ ቀላል አይደለም።

መ፥ 'ይህ እያደገና ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ልምምድ ነው።'

በእርግጥ ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ እየተስፋፋ የመጣ ልምምድ ነው። ተቀባይነት ማግኘት ያለማግኘቱ ግን ሌላ ነገር ነው። በዚህ ባለንበት ዘመን ደግሞ አንዴ ይወለድ እንጂ ከዚያ በኋላ የማያድግ ነገር የለም። አንድ ትምህርት ይጀመር እንጂ ተቀባዮች አያጣም። እያደገ የመጣ እንቅስቃሴ ሁሉ ግን ሊቀበሉት የተገባ ነው ማለት ስሕተት ነው።

ሠ፥ 'የሚታዩ ምልክቶችስ?'

በመጀመሪያ ድንቅና ምልክቶች ወይም ተአምራት ቢከሰቱ የእነዚህ ነገሮች ምንነትና ለምንነት መፈተን አለበት። ከመመርመር ይልቅ አይቶ ብቻ መደነቅ ክርስትና ሳይሆን ጅልነት ነው። ምልክቶች የትክክለኛ ሃይማኖትና እንቅስቃሴዎች ማረጋገጫ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም። ምክንያቱም ሰይጣንም ምልክቶችንና ተአምራትን ሲሠራ ኖሮአል። በመጨረሻው ዘመንም ይህ እንደሚሆን በቃሉ ውስጥ በበቂ ዝርዝር ተጽፎ ይገኛል። እግዚአብሔር ተአምራትን የሚያደርግ አምላክ ነው ማለት ተአምራት ሁሉ ከእርሱ ናቸው ማለት አይደለም። ስለዚህ በአንዳንድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተአምራትና ምልክቶች ቢታዩ ሁሌም እግዚአብሔር እንዳደረገ ማሰብ ትክክል አይደለም።

ረ፥ 'እነ እገሌና እገሌ አሉበት።'

የምናውቃቸው ወይም የሚቀርቡን ሰዎች በኛ ላይ የሚያደርሱት ገንቢም አፍራሽም ተጽእኖ አለ። በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ወይም የጓደኞቻችን በነዚያ ልምምዶች ውስጥ መገኘት ያለ ብዙ ትግል ወደዚያ ለመሄድ የሚፈጥረው ጫና አለ። የቡድን





ግፊትና ስበት በአቅጣጫችን የፊት እርምጃ ላይ ለውጥ ለመፍጠር ይችላል። ጓደኞችን ላለማጣት ወይም እነርሱ ከእኔ ይበልጣሉና እነርሱን በጆሮ ለመስማት ብሎ ኀሊናን ደፍኖ የሚገቡበት አዘቅት ኋላ በቀላሉ የማይወጡት ይሆናል። ለሌሎች ድንበር የሌለው ጆሮ ሰጥቶ መስማት፥ ይሉኝታና፥ ከቡድን የመውጣት ፍርሃት ተመልሰው የማያስተካክሉትን አደጋ ያስከትላል።

ይህ ሌሎችን በመስማት የሚገቡበትን አደጋ የሚያሳይ አንድ ታሪክ እነሆ፤ ሚኒያፖሊስ በምትባል የአሜሪካ ከተማ አጠገብ በሚያልፍ አንድ መንገድ የሚያቋርጥ የባቡር ሐዲድ ላይ በ1998 የተፈጸመ አደጋ ነበረ። ሐዲዱ በአንድ ጊዜ ሁለት ባቡሮችን የሚያስኬድ ድርብ ሐዲድ ያለው ነው። ባቡር በመምጣት ላይ መሆኑን የሚያስጠነቅቀው መብራት እንደበራና የደወል ድምጽም መሰማት እንደጀመረ መኪናዎች ቆሙ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ግዙፉ የዕቃ መጫኛ ባቡር ፉርጎዎቹን አስከትሎ መጥቶ አልፎ ሄደ። ከሄደ በኋላ እንደ ግዛቲቱ የአነዳድ ሕግ መሠረት መብራቶቹ እስኪጠፉና የደወሉም ድምጽ ጸጥ እስኪል ድረስ መጠበቅ አለበት። ባቡሩ ግን አልፎ ከሄደ በኋላም መብራቱ አልጠፋም ድምጹም ጸጥ አላለም። ከፊት እመንገዱ ላይ መኪና ውን ያቆመው ሰው እንዲሄድላቸው ከኋላ ያሉት ሰዎች ጥሩምባ መንፋት ጀመሩ። ጆሮ የሚዘነጥሉ የጥሩምባ ዓይነቶች፥ የሰዎችም ጩኸትና እጅ በማወራጨት ምልክትም ከፊት ያለው ሰው እንዲሄድላቸው መናገር ጀመሩ። ሰውየው ግን እጆቹን የመኪናው መሪ ላይ አድርጎ ዝም ብሎ ተቀመጠ። የጥሩምባዎቹንና የሰዎቹን ጩኸት መቋቋም ሲያቅተው ግን ቀስ ብሎ ተነሥቶ ወደ ፊት መሄድ ጀመረ። ልክ ሐዲዱን እያቋረጠ ሳለ የመጀመሪያው ባቡር ከሄደበት አቅጣጫ የሚመጣ ፈጣን የመንገደኞች ባቡር መጥቶ ያቺን እያቋረጠች ያለች መኪናና በውስጧ ያለውን ሰው በሁለት ወይም ሦስት ሴኮንዶች ውስጥ በባቡሩ ሕጋዊ መንገድ ውስጥ ብትንትን አድርጎ ጣላቸው። ያ ሰው ከተገለጠው ሕግና ሊደርስ ከሚችለው አደጋ ይልቅ ሰዎችን ስለፈራ ራሱን ወደ አስፈሪ መቅሰፍት ውስጥ ወረወረ። ምሳ. 29፥25 ሰውን መፍራት ወጥመድ መሆኑን ይናገራል።

ከላይ ያየናቸው ተቀባይነት ያገኙ ስህተቶች ናሙናዎች ናቸው። እነዚህን የመሳሰሉ ተደጋግመው የሚቀርቡ ትክክለኛ ያልሆኑ ምክንያቶች ይኖራሉ። አንዳንዴ መደጋገማቸው እውነት ያስመስላቸዋል። ሌላ ጊዜም በአሻሚና ግልጽ ባልሆኑ ቃላት መጠቅለላቸው ተቀባይ ያስገኝላቸዋል።